ጎንደር ዩኒቨርሲቲ
የማኅበራዊ ሳይንስና ሂውማኒቲስ ፋክልቲ
የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ሥነጽሑፍ- አማርኛ ትምህርት ክፍል

# የግእዝ ቋንቋ ማስተማሪያ ጽሑፍ

# (Handout)

| | |
|---|---|
| የትምህርቱ መጠሪያ | መሠረታዊ ግዕዝ |
| የትምህርቱ መለያ ቁጥር | Elam 2072 |
| የክሬዲት መጠን | (4) 7 ECTS |
| መርሃ ግብር | BA ድግሪ |
| ወሰነ ትምህርት | ሁለተኛ አመት ሁለተኛው ወሰነ ትምህርት |

ሚያዝያ 2012


AbeselomNekatibeb(nabeselom@gmail.com)

## አጠቃላይ መግለጫ (Description)

ይህ የማስተማርያ ጽሑፍ በአምስት ምእራፎች የተከፈለ ሲሆን፣ምእራፍ አንድ የግእዝ ቋንቋ እድገት፣ ምንነትና ታሪክ፣ ከሴም ቋንቋ ጋር ያለው ዝምድና፣ የግእዝ ፊደላት መሰረታዊ ለውጥና የመሳሰሉትን ይዟል። ምእራፍ ሁለት ደግሞ የግእዝ ቋንቋ ስነ-ድምፅንና ሥርአተ ንባብን የያዘ ሲሆን፣ ምእራፍ ሦስት ክፍላተ ቃል፣ ተውላጠ ስም፣ ቅጽል፣ አንቀዝ ግስና የግስ እርባታ፣ አገባባት (ተውሳከ ግስ፣ መስተዋድድ፣ እና መስተጻምር) ይዞ ይገኛል። ምእራፍ አራት የዐረፍተ ነገር አይነትና መዋቅር ሲይዝ፣ ምእራፍ አምስት ተግባራዊ ሰዋሰው (ምንባባት) አካቶ የያዘ ነው።

(ምእራፍ) (ገጽ)

ምዕራፍ አንድ------------------------------------------------------------------------------------------2
ምዕራፍ ሁለት-----------------------------------------------------------------------------------------7
ምዕራፍ ሦስት----------------------------------------------------------------------------------------10
ምዕራፍ አራት----------------------------------------------------------------------------------------48
ምዕራፍ አምስት--------------------------------------------------------------------------------------52
- ዋቢ መጻሕፍት------------------------------------------------------------------------------58

### የኮርሱ ዓላማ ፡-

### ተማሪዎች ይህን ኮርስ ከአጠናቀቁ በኃላ፡-

- የግእዝ ቋንቋን እድገትና ታሪክ ያስረዳሉ፤
- የፊደላቱን ጠቀሜታ በተገቢው መንገድ ይለያሉ፤
- የግእዝን ፊደላት አመጣጥና ከሴም ቋንቋዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ያስረዳሉ፤
- የግእዝን አንዞች አገባብ ይዘረዝራሉ፣ ለይተውም ይጽፋሉ፤
- ነባርና ውልድ ስሞችን፣ ተውላጠ ስሞችንና ቅጽሎችን ይገነዘባሉ፤
- የግስ ርባታና የግስ ዓይነቶችን ይለያሉ፤
- የግእዝ ቋንቋ ተውሳከ ግሶችን፣ አያያዦችንና መስተዋድዶችን ይለያሉ፤የግእዝ ቋንቋን የዓረፍተ ነገር ዓይነቶችና የቃላት አቀማመጥ ይለያሉ፤
- በግእዝ ጽሑፎችን በመጻፍ ከግእዝ ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ይተረጉማሉ፤ቀላል ዓረፍተ ነገሮችን፣ ይገነዘባሉ፤


AbeselomNekatibeb(nabeselom@gmail.com)

# ምዕራፍ አንድ

## ፩. የግእዝ ቋንቋ አመጣጥና ዕድገት

ኢትዮጵያ ከደቡብ ሰሀራ ሀገራት መካከል የጥንታዊ (ስነጽሑፍ) ቋንቋ ባለቤት ናት። ይህም በዘመነ አክሱም ይነገር የነበረው የግእዝ ቋንቋ ነው። ግእዝ በኢትዮጵያ ቀዳሚ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ በመሆኑ ያልዳሰሰው የዕውቀት ዘርፍ የለም። ብዙ የትርጉም ሥራ ሠርቶበታል፤ መንፈሳዊ ድርሳናት ተደርሰውበታል፣ የሀገርና የሕዝብ ታሪኮች፤ የነገሥታት ዜና መዋዕሎችና የፍልስፍና መጻሕፍት ተዘግበውበታል፡፡ በመሆኑም ግዕዝ ለኢትዮጵያ የውበት፣ የታሪክ፣ የባህል፣ የወግ ፣ የሥልጣኔም መሠረት ነው።

ግእዝ የማን ቋንቋ ነው?

ግእዝ ከየትኛው የቋንቋ ግንድ እንደተገኘ በምሁራን መካከል የተለያየ አሳብ አለ። የሶቭየት ተማራማሪዎች ለምሳሌ ኤቢ. ዶጎብልስኪ እና ኢጎር ዲያክፍኖት ግእዝ የመጀመሪያዎቹ የአፍሪቃውያን/ኩሻውያን/ ቋንቋ ነው ሲሉ ይሞግታሉ። ይህንን አሳብ የሚጋሩ የአገር ውስጥም ከአገር ውጪም የተነሡ በርካታ ሊቃውንት አሉ፡፤ ለዚህ የሚያቀርቡትም አመክንዮ ከአፍሮ እስያ ቋንቋዎች ብዙዎቹ የሚገኙት በኢትዮጵያ ነው ከሚል መነሻ ነው። ሌሎች ወገኖች ግእዝን ሴማዊ ቋንቋ ሲያደርጉት ኤ መርቶኔንና ሊኦኔል ቤንደር ከውጭ አገር ሰዎች ከአገር ውስጥ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ይጠቀሳሉ።

በሥነ ልሳን ጥናት መሠረት የግዕዝ ቋንቋ ቀዳሚ ከሚባሉት ሴማውያን ልሣናት አንዱ ሲሆን ምድቡም ከደቡባዊ የሴም ቋንቋ ቤተሰብ ውስጥ ነው። በኢትዮጵያም ሰሜናዊ ኢትዮ-ሤማዊ ምድብ ስር ይገኛል፡፡

| ሰሜን ኢትዮ-ሤማዊ | ደቡብ ኢትዮ-ሤማዊ |
|---|---|
| ግእዝ | አማርኛ |
| ትግረ | አርጎብኛ |
| ትግርኛ | የጉራጌ ቋንቋዎች |
| | ጋፋት |
| | አደሬኛ |

በኢትዮጵያ ታሪክ ሙሉ ለሙሉ በአማርኛ ከመተካቱ በፊት ግዕዝ የሀገራችን ብሔራዊ ቋንቋ ሆኖ ለብዙ ምእት ዓመታት አገልግሏል። ግዕዝ እስከ 19ኛው መ/ክ/ዘ ድረስ የሀገሪቱ ልሣነ ታሪክ እና

የጽሑፍ ቋንቋ ሆኖ ያገለገለ ሲሆን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ ግን ከጥንት እስካሁን ድረስ የአገልግሎትና የትምህርት ቋንቋነቱ እንደቀጠለ ነው።

ፊደል እና ጽሑፍ ሲነሳ ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀዳሚ ቦታ እንድትይዝ ያደረጋት ግዕዝ ስለሆነ የብዙዎችን ቀልብ ስቧል። በተለይ ደግሞ በግዕዝ ቋንቋ ተጽፈው የሚገኙ እጅግ በርካታ የሆኑ የብራና ጽሑፎች ዓይነት እና ይዘት የአገሬውንም የውጭውንም ምሁራን ትኩረት እንደሳቡ ናቸው። የግዕዝ ቋንቋ ሥነ ድምጽ፣ ሥነ መዋቅር እና ሥነ ምዕላድ ባጠቃላይ የቋንቋው ሰዋስዋዊ ሒደት፤ የጽሑፎቹ ዘመን ተሻጋሪነት፣ የይዘት ብስለትና ኅብረ ብዙነት፤ እንዲሁም የጸሐፊዎቹ ትጋት እና ጥንቃቄ በእጅጉ የሚደነቅ ነው።

## <u>፩.፩ የግእዝ ቋንቋ ምንነት</u>

ግእዝ የሚለው ቃል በውስጡ በሚይዛቸው ፊደላት ምክንያት የተለያዩ ምሁራን የተለያየ ብያኔና ስያሜ ሲሰጡት ይስተዋላል፡፡

*ግእዝ የሚለው ስም ገአዘ ወይም ግእዘ ከሚለው ቀዳማዊ አንቀጽ (ሥርወ ቃል) የወጣ ሲሆን ትርጉሙም መጀመርያ፣ አንድ፣ አንደኛ፣ ማለት ነው።*

- *አንድም ግእዝ ማለት ከሁሉ በፊት፣ ቀዳማዊ ማለት ነው።*
- *አንድም ግእዝ ማለት ስመ ተፀውዖ (የመጠርያ ስም )፣ የቋንቋ ወገን፣ ልዩ ክፍል ማለት ነው (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ 1948÷29 ፣ 294 )።*

*ግእዘ አዘነ፣ ተቆጣ፣ ተበሳጨ፣ ማለት ሲሆን፣ ግእዝ ማለት አመል ፀባይ፣ ልማድ፣ ወዘተ.፡፡*

- *አንድም ግእዘ ኢጋዘ፣ተማረ፣ቆጠረ ማለት ሲሆን፣ግእዝ ማለት መጀመሪያ፣ የፊደል ስም፣ የዜማ ስም ነው፡፡*

ከላይ እንደተገለጸው ግእዝ የሚለው ቃል በውስጡ በሚይዛቸው ድምፆች መቀያየር ምክንያት የተለያየ ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ይህም ግዕዝ የሚለው ቃል በዐይኑ "ዐ" ሲጻፍ ነጻነት ማግኘትን፤ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መጓዝን፤ የጊዜ መለዋወጥን ሁሉ ያመለክታል፡፡

ቀደም ያሉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ነገደ ሐበሻት በ፲ኛው ምእተ ዓለም ሳባ ከሚባል ደቡባዊ ዐረብ አውራጃ በመነሳት በባብል መንድብ አድርገው ወደ ኢትዮጵያ በመግባት በአክሱም እና አካባቢዋ መኖር እንደ ጀመሩና ኢትዮጵያም በስማቸው አቢሲኒያ ተብላ እንድትጠራ እንዳደረጓት ይገለጻል፡፡ እንዲሁም ከሐበሻት በኃላ ወደኢትዮጵያ የገባው ነገደ ሄም አግዓዚ ሲሆን፣ የአግዓዝያንም ቋንቋ ሌሎች የሳባውያን ቋንቋ አድክሞ ጠንካራ

ቋንቋ ለመሆን ቻለ፡፡ አግዓዝያንም ሀገራቸውን ብሔረ አግዓዚ አስብለው ቋንቋቸውን ግእዝ አሰኝተዋል፡፡[1]

ባጠቃላይ ግእዝ ፫ሺ.ሀ ዘመን ያስቆጠረ ከመሆኑም በላይ፤ በዘመነ አክሱም ብሔራዊና ዓለማቀፋዊ የነበረና ኢትዮጵያን በዓለም የሥነ ጽሑፍ መድረክ ያስተዋወቀ በኢትዮጵያ ቀዳሚ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋ ነው፡፡

## ፩.፪. ግእዝ ከደቡብ ዐረብያ ቋንቋ ጋር ያለው ግንኙነት

ቀደም ባሉ ጥናቶች መሠረት ሳባዊ ቋንቋ በደቡብ ዐረብ (የመን) ይነገር የነበረ ቋንቋ ሲሆን፣ ፳፱ ፊደላት አሉት፡፡ ግእዝም ከሳባ ቋንቋ ፊደሉን እንደ ወሰደ ይታመናል፡፡ ግእዝ ከ፳፱ የሳባ ፊደላት ፫ቱን ትቶ ፳፬ቱን ፊደላት ብቻ ወስዷል፡፡ ሁለት ፊደላትን (ጰ፣ ፐ) ደግሞ ከሌላ ቋንቋ (ከግሪክ ቋንቋ) በመውሰድ ቁጥሩን ወደ፳፮ ከፍ እንዲል አድርጓል፡፡ ግእዝ የተዋቸው ፫ቱ የሳባ ፊደላትና የወሰዳቸው ፳፬ቱ የሳባ ፊደላት የሚከተሉት ናቸው፡፡

### ፩.፪.፩ ግእዝ ከሳባ የወሰዳቸው ፊደላት

| የሳባ ፊደል | የግእዝ ፊደል | የሳባ ፊደል | የግእዝ ፊደል | ያልተወሰዱት የሳባ ፊደላት |
|---|---|---|---|---|
| 𐩱 | አ | 𐩺 | የ | 𐩪 𐩻 𐩶 𐩹 𐩼 |
| 𐩨 | በ | 𐩫 | ከ | |
| 𐩴 | ገ | 𐩣 | መ | |
| 𐩵 | ደ | 𐩬 | ነ | |
| 𐩠 | ሀ | 𐩦 | ሠ | |
| 𐩭 | ኀ | 𐩲 | ዐ | |
| 𐩷 | ጠ | 𐩤 | ቀ | |
| 𐩸H | ዘ | 𐩳 | ፀ | |
| 𐩢 | ሐ | 𐩰 | ፈ | |
| 𐩥 | ወ | 𐩮(Ж) | ጸ | |
| 𐩧 | ረ | 𐩡 | ለ | |
| 𐩩 | ተ | 𐩯 | ሰ | |

[1] የቅርብ ጊዜ ጥናቶች እንደሚያስረዱት ሤማዊ ቋንቋ በጥንታዊ ደቡብ ዐረብያ ከመገኘቱ በፊት በአፍሪካ ቀንድ ፪ሺ.ሀ ዓመት ቀድሚያ የነበረው ሲሆን፣ ነገደ ሤም ሆኑ የኢትዮጵያ ሤማዊ ቋንቋዎች ከዐረብያ የመጡ ሳይሆኑ ኢትዮጵያ የነበሩ ናቸው፡፡ በተቃራኒው የሤም ቋንቋዎች ከኢትዮጵያ ወደ የመንና የመሳሰሉት ሄደዋል፡፡ ኢትዮ ሤማዊ ብቻ ሳይሆኑ የሤማውያን መነሻ ቋንቋ (Proto-Semitic) እና የአፍሮ እስያ (Afro-Asiatic) የቋንቋ ቤተሰብ መፈጠሪያ ምንጫቸውን ኢትዮጵያ አድርገው ወደ መካከለኛው ምሥራቅና ወደመሳሰሉት ተሰራጭተዋል የሚል ነው፡፡


AbeselomNekatibeb(nabeselom@gmail.com)

## ፩.፫. በግእዝ ላይ የተደረገ መሠረታዊ ለውጥ

ግእዝ የዛሬውን መልክና ቅርፅ ከመያዙ በፊት በተለያዩ ለውጦች ውስጥ አልፎአል፡፡ ግእዝ ካደረጋቸው ለውጦች መካከል ዋና ዋናዎቹ ፩. የአጻጻፍ አቅጣጫ ለውጥ፤ ፪. የፊደላት ቅደም ተከተል ለውጥ፤ እና ፫. የአናባቢ አጻጻፍ ጥቆማ መዘጋጀት ናቸው፡፡

### ፩.፫.፩ የአጻጻፍ አቅጣጫ ለውጥ

የግእዝ ፊደል ይጻፍ የነበረው እንደ ሌሎቹ ሤማዊ ቋንቋዎች (ሳባ፣ ዐረብኛ፣ ዕብራይስጥ) ከቀኝ ወደ ግራ የነበረ ሲሆን፣ የአጻጻፉም ዘይቤ “የበሬ እርሻ” ይመስላል፡፡ ሆኖም በ፫፻ዓ/ም ከግራ ወደቀኝ እንዲሆን ተስተካክሏል፡፡

### ፩.፫.፪ የፊደላት ቅደም ተከተል ለውጥ

የግእዝ ፊደላት ቅደም ተከተል አ በ ገ ደ…የነበረውና ሲሆን፣ በ፫፻፳ዓ/ም ቅደም ተከተላቸው በ ሀ ለ ሐ መ… ተለወጠ፡፡ ፊደላቱ ለአኃዝ ያገለግሉ ስለነበር ቅደም ተከተል ተዛባ፡፡ በመሆኑም ለቁጥሮቹም አዲስ ምልክት ተዘጋጀላቸው (፩ ፪ ፫ ፬ ፭ ፮…)፡፡ አዲሶቹ የግእዝ ቁጥር ምልክቶች ከግሪክ ፊደላት እንደ ተወሰዱ በብዙ ምሁራን ዘንድ ይታመናል፡፡

### ፩.፫.፫ የአናባቢ አጻጻፍ ጥቆማ ማዘጋጀት

የግእዝ ፊደል የዛሬውን ቅርፅ ከመያዙ በፊት ይጻፍ የነበረው በተነባቢ ብቻ ነበር፡፡ (ለምሳሌ፡-ግእዝ በተናባቢ ተጽፎ በመጠራ (ኤርትራ) ሐውልት ላይ ይገኛል(ዘሐወለተ ዘአገበረ አገዘ ለአበወሀ፡፡ በአሁኑ ግእዝ አነጋገር⇒ዝ ሐውልት ዘአግበረ አገዘ ለአበዊሁ)፡፡ ሆኖም በ፬ኛው መ /ክ/ ዘመን ተነባቢን ከአነባቢ ጋር መጻፍ ተጀመረ፡፡

### ፩.፫.፬ ሞግሼ (ተቀራራቢ ድምፅ ያላቸው) ፊደላት

ግእዝ ፳፮ መሠረታዊ ፊደላት ሲኖሩት እያንዳንዱ የራሱ የሆነ ድምፅ አለው፡፡ ይሁን እንጂ ካሉት ፳፮ ፊደላት መካከል ሦስት [ሀ፣ ሐ፣ ኀ]፣ ሁለት [ሠ፣ ሰ] ፣ ሁለት [አ፣ ዐ]፣ ሁለት [ፀ፣ ጸ] በተመሳሳይ ድምፅ ይገኛሉ፡፡ እነዚህም በጊዜ ሂደት የመጀመሪያ ድምፃቸውን ለቀው ተመሳሳይ ድምፅ እንደያዙ ይታመናል፡፡ ሆኖም እነዚህ ፊደላት በግእዝ ድምፃቸው ቢጠፉም በቅርፅ፣ በትርጉም (በአጻጻፍ) ልዩነታቸውን እንደጠበቁ ይገኛሉ፡፡ የትርጉም (የአጻጻፍ) ልዩነት እንደሚከተለው ነው፡፡

| ሰ፣ሠ | አ፣ዐ እና ፀ ፣ ጸ | (ሀ፣ሐ፡ኀ) |
|---|---|---|
| ሰ- ሰአለ=ለመነ<br>ሠ-ሠዐለ=ሥዕል ሣለ<br>ሰ-ሰረቀ=ሰረቀ→ለሌባ<br>ሠ-ሠረቀ= ወጣ→ለፀሐይ | አ-አመት =ሴት አገልጋይ<br>ዐ-ዓመት=ዘመን፣ ጊዜ | ሐ-መሐረ=ማረ፣ ይቅር አለ<br>ሀ- መሀረ =አስተማረ<br>ኀ- ኀለየ=ዘመረ፣ ዘፈነ<br>ሐ- ሐለየ= አሰበ |
| | ፀ-ፀሐይ =ፀሐይ<br>ጸ-ጸሎት=ጸሎት | |

# ምዕራፍ ሁለት

## ፪. ሥነ ድምፅ

ማንኛውም ቋንቋ መሠረቱ ድምፅ ነው፡፡ የንግግር ድምጾች በሰው አንደበት ብቻ የሚፈጠሩ ስለሆኑ ድምፀ ልሳናት ተብለው ይጠራሉ፡፡ በአንደበት የሚፈጠሩ ድምፆች ተናባቢ እና አናባቢ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

### ፪.፩ ተናባቢ ድምፆች

ተናባቢ ድምፆች በአንደበት አካል ንክኪ አማካኝነት የሚፈጠሩ ድምፆች ናቸው፡፡ ድምፆች እንዲፈጠሩ የሚያደርጉ የአካል ክፍሎች ከናፍር ፣ጥርስ፣ ድድ፣ ላንቃ፣ ትናጋ፣ እንጥል፣ ምላስ፣ ጉሮሮና ማንቁርት ናቸው፡፡

| | a | u: | i: | a: | e: | (ə) | o: |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| h | ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| l | ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ḥ | ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| m | መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| s | ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| r | ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| š | ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| q | ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| b | በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| t | ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ḫ | ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| n | ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ʾ | አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |

| | a | u: | i: | a: | e: | (ə) | o: |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| k | ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| w | ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ʿ | ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| z | ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| y | የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| d | ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| g | ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ṭ | ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| p̣ | ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ṣ | ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ḍ | ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| f | ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| p | ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

**ዲቃላ/ዝርዋን/ ፊደላት (Labiovelars)**


| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| $g^w$ | ጐ | ጕ | ጕ | ጓ | ጔ |
| $k^w$ | ኰ | ኵ | ኵ | ኳ | ኴ |
| $q^w$ | ቈ | ቍ | ቍ | ቋ | ቌ |
| $ḫ^w$ | ኈ | ኍ | ኍ | ኋ | ኋ |

## ፪.፪ አናባቢ

አናባቢዎች የሚፈጠሩት ያለ አካላት ንክኪ ሲሆን፤ አፋዊና ነዛሪ ናቸው። የግእዝ ቋንቋ አናባቢ ድምፆች ሰባት ሲሆኑ እነርሱም፡- “ኧ፣ ኡ፣ ኢ፣ ኣ፣ ኤ፣ እ፣ ኦ” ናቸው፡፡ አናባቢዎች በአንድ ተወከሉ እንጂ ከተናባቢ ተነጥለው አይፃፉም ድምፃቸውም የቅንጅት ውጤት ነው፡፡

### ፪.፪.፩ የአናባቢ ድምፆች መካነ ንባብ

አናባቢዎች አፈጣጠራቸው በምላስና በከንፈር እንቅስቃሴ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡




ለአናባቢዎች መፈጠር ምላስ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አለው። በምላስ እንቅስቃሴ የሚፈጠሩት ድምፆችን የፊት፣ የኋላ፣ የመሐል በማለት በሦስት መመደብ ይቻላል፡፡ ተንቀሳቃሹ ክፍል የሚገኙበትን ከፍታ (ዝቅታ) መሠረት በማድረግ የላይ፣ ልከኛና የታች ተብለው ይመደባሉ፡፡

## ፪.፫. ሥርዓተ ንባብ

የግእዝ የንባብ መንገድ በአራት ዋና የንባብ ዐይነቶች ይነገራል፡፡ እነዚህ የንባብ ዐይነቶች ተነሽ፣ ወዳቂ፣ ተጣይ እና ሰያፍ ናቸው፡፡

ተነሽ፡-በግእዝ፣ በካዕብ፣ በሣልስ፣ በራብዕና ሳብዕ ፊደል እየደረሰ መድረሻውን ፊደል በማንሣት ይነበባል፡፡ አብዛኞቹ ተነሽ ንባቦች ከግስ እና ከግስ የተመሠረቱ ቃላትን ያጠቃልላል፡፡

ምሳሌ፡- መጽአ፣ ንዑ፣ ሑሪ፣ ንግራ፣ ሀቦ፣ ሕይወተ፣ ገበርክሙ

- መጽአ ኀቤነ
- ቆመ ወነበረ

ወዳቂ፡-በግእዝ፣ በካዕብ፣ በሣልስ፣ በራብዕ፣ በኀምስ፣ በሳድስ፣ በሳብዕ ፊደላት ሲደርስ መድረሻ ፊደሉን ይዞ ወዳቂ በማድረግ ወድቆ ይነበባል፡፡ምሳሌ፡-አሐተ፣ ዝንቱ፣ መሓሪ፣ ዕዝራ፣ ውዳሴ፣ እምዝ፣ ውቅሮ፣ ቀተሎ፣ ብእሲ፣ ቀዲሙ ወዘተ.፡፡

- መሓሪ ውእቱ
- ረከበ ውዳሴ

ተጣይና ሰያፍ፡-ተጣይና ሰያፍ በሳድስ ፊደል ብቻ ይደርሳሉ፡፡ ተጣይ ንባብ የመድረሻውን ተከታይ ፊደል ያዝ በማድረግ ጣል ብሎ ይነበባል፡፡

ምሳሌ፡-ተጣይ→ሕይወት፣ ሞት፣ ወርቅ፣ ሊቃውንት፣ ሢመት፣ ባሕር፣ ኅብስት፣ ወዘተ. በአብዛኛው ስሞች ናቸው፡፡

- ሕይወት ወሞት

ሰያፍ፡-የሰያፍ ንባብ መድርሻ ሳድስ ቀለም ነው፡፡ ይህም የግስና የተጸውዖ ስምን ያጠቃልላል፡፡ አነባበቡም እንደ ተነሽ ንባብ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሰያፍ→አማኑኤል፣ የሐውር፣ ይቀትል፣ ትትሐነጽ፣ ገብርኤል፣ አቤል፣ ጴግሮስ፣ ወዘተ.

- ወይሰመይ ስሙ አማኑኤል …ወዘተ.፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## ፫. ክፍላተ ቃል

ክፍላተ ቃል በቅርፅ፣ በአገባብና በዐረፍተ ነገር ውስጥ በሚይዙት ቦታ ተመሳሳይነት ወይም ልዩነት በግእዝ በሰባት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ፡፡ እነርሱም፡-

፩. ስም (ነባርና ዘር)
፪. ተውላጠ ስም
፫. ቅጽል
፬. ግስ
፭. ተውሳከ ግስ
፮. መስተዋድድ
፯. መስተፃምር

### ፫.፩ ስም (ነባርና ዘር)

ስም ሰመየ ከሚለው ግስ የወጣ ሲሆን ስም አወጣ ማለት ነው፡፡ ስም የሚለው ቃል ደግሞ ጥሪ፣ መጠሪያ፣ መለያ፣ መጥሪያ ማለት ነው፡፡ ማንኛውም ነዋሪ የሚጠራበት ቃል ስም ይባላል፡፡ በግእዝ ነባር፣ ዘርና ጥሬ ዘር የሚባለው ሁሉ ተጠቅሎ ስም (ጥሬ ዘርእ ሰዋስው) ተብሎ ይጠራል፡፡ ስም እንደ ባሕርዩ ነባርና ውልድ ስም ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡

#### ፫.፩.፩ ነባር ስም

ነባር ስም ከግስ ርባታ የማይገኝ ለግስ ርባታ ዘርእ የማይሆን ነባር ቃል ነው። ወይም ከዘርእና ከአንቀጽ የማይገኝ ትርጓሜው የማይለወጥ ራሱን ችሎ የሚነገር ቃል ነው። ለምሳሌ፡-ማይ፣ ኮከብ፣ አንበሳ፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ሀሉ ዘርነት የሌላቸው ከዘርእ የማይገኙ ስለሆነ ነባር ይባላሉ፡፡

#### ፫.፩.፩. የመጠሪያ ስም

በተናጠል ወይም በጥቅል የሚነገር የስያሜ ቃል የመጠሪያ ስም/ስመ ተጸውዖ ይባላል፡፡ አብዛኞቹ መጠሪያ ስሞች ከነባር ስሞች ጋር የሚሰለፉ ሲሆን ጥቂቶቹ ከግስ ርባታ የሚገኙ ናቸው፡፡ የመጠሪያ ስሞች በአራት ንኡሳን ክፍሎች ይመደባሉ፡፡ እነርሱም፡-

<u>**፩. ስመ ተጸውዖ (የመጠሪያ ስም)፡-**</u> ስመ ተጸውዖ ውስጠ ብዙነት የሌለው አንድ ሰው ወይም ነገር የሚጠራበት የግል ስም የያዘ ነው፡፡ ለምሳሌ፡-ደስታ፣ ሐጎስ፣ አዋሽ፣ ገመቹ፣ ጎንደር፣ ዳሽን ወዘተ. ናቸው፡፡

<u>**፪. ስመ ኵሉ ( የወል ስም)፡-**</u> ስመ ኵሉ  የሚባለው በተፈጠሮ አንድ ዐይነት የሆኑ ነገሮች በጠቅላላው የሚጠሩበት የጋራ ስም ነው፡፡ የወል ስሞች የቁጥር አመልካች ምዕላድ ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ በዚህም ከጥቅል ስም ይለያሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ብእሲ፣ ብእሲት፣ ላህም ፣ አንበሳ፣ ወዘተ.፡፡

<u>**፫. ስመ  እንግልጋ  (የጥቅል ስም)፡-**</u> ስመ እንግልጋ  ውስጠ ብዙነት ያለው ሆኖ በአንድና በብዙ የሚነገር ጠቅላይና አንድ ስብስብ የሚጠራበት ክፍል ነው፡፡ ወይም ነገሮች በአንድነት ተጠቃለው በአንድ ቦታ ላይ ሲገኙ በጅምላ የሚጠሩበት ስም ነው፡፡ የብዙ ቁጥር አመልካች ምዕላድ አያስከትሉም፡፡ በዚህም ከወል ስም ይለያሉ፡፡

<table>
<tr><td rowspan="2">ሰብእ<br>ሕዝብ<br>ሐራ</td><td>ነጠላ = መጽአ ሰብእ<br>ነጠላ = ሖር ኀነበ ዝንቱ ሕዝብ</td><td>ብዙ= መጽኡ ሰብእ<br>ብዙ= አበሱኒ ሕዝብከ</td></tr>
<tr><td colspan="2">ማኅበር</td></tr>
</table>

አሕዛብ  በብዙ አንቀጽ ይነገራል እንጂ በነጠላ አንቀጽ አይነገርም፡፡

- ለምሳሌ፡- አሕዛብ ገብሩ ግብረ፡፡

<u>**፬. ስመ ረቂቅ ፡-**</u> ስመ ረቂቅ በዐይን ሊታዩ የማይችሉ እና አንድ ሁለት ተብለው ሊቆጠሩ የማይችሉ ነገር ግን በአእምሮ ብቻ የሚታሰቡ ነገሮች የሚጠሩበት የስም ንኡስ ክፍል ነው፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን ረቂቅ ስሞች እንመልከት፡፡ ፍቅር፣ ሞት ፣  አምላክ ፣ ቅድስና፣ ሕይወት፣ ወዘተ.

### <u>፫.፩.፪. ውልድ ስም (ዘርእ)</u>

ውልድ ስም ከግስ ርባታ የሚገኝ ስም ነው (ምሳሌ፡-ብርሃን→በርሀ ከተባለው ግስ የተገኘ ውልድ ስም)፡፡ ከግስ የሚወለዱ ውልድ ስሞች (የስም ክፍሎች) በአራት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም፡- ዘመድ ዘርእ፣ ባዕድ ዘርእ፣ ምዕላድ ዘርእ እና  ባዕድ ከምዕላድ ዘርእ ናቸው፡፡

<u>**ዘመድ ዘርእ፡-**</u> ዘመድ ዘርእ የሚባለው ግሱን መስሎ የሚወጣ ወይም የሚገኝ ስም ነው (ግሱን የመሰለ ማለት ነው)፡፡ እንደ ዘመድ ዘርእ ሁሉ ባዕድ ቀለም ሳይጨም በኃምስ፣ በራብዕ፣ በሳብዕ የሚደርስ ቃል (ስም) ጥሬ ዘርእ ይባላል፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| ግስ | ዘመድ ዘርእ | ትርጉም |
|---|---|---|
| ቀተለ<br>ገብረ<br>ለበወ | ቀትል<br>ግብር<br>ልብ | ግድያ<br>ሥራ<br>ልብ |

<u>በዕድ ዘርእ፡-</u> ባዕድ ዘርእ ቅድመ ምዕላድ ያለው፣ በግሱ እግር የሌለ ፊደል የያዘና በባዕድ ፊደል የሚነሣ ስም ነው፡፡ ለምሳሌ በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ውልድ ስሞች እንመልከት፡፡

| _ግስ | ባዕድ ዘርእ | ትርጉም |
|---|---|---|
| ኰነነ<br>ጸሐፈ<br>ዘመረ | መኰንን<br>መጽሐፍ<br>መዝሙር | ገዥ<br>መጽሐፍ<br>መዝሙር |

<u>ምዕላድ ዘርእ፡-</u> ምዕላድ ዘር በቃሉ መድረሻ በግሱ እግር የሌለ ፊደል ሲገኝ ነው ይህም ድኅረ ምዕላድን በማስገባት የምናገኘው ነው፡፡ የድኅረ ምዕላድ ፊደላት (ን፤ዊ፤ት) ናቸው፡፡

| ግስ | ምዕላድ ዘርእ | ትርጉም |
|---|---|---|
| በርሀ<br>ቀነወ<br>ሐመየ | ብርሃን<br>ቀኖት<br>ሐሜት | ብርሀን<br>ምስማር<br>ሐሜት |

<u>ባዕድ ከምዕላድ ዘርእ፡-</u>በባዕድ ተነሥቶ በባዕድ የሚጨርስ ስም ነው (ድኅረ ምዕላድንና ቅድመ ምዕላድን የያዘ ስም ነው)፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን ውልድ ስሞች እንመልከት፡፡

| ግስ | ባዕድ ከምዕላድ ዘርእ | ትርጉም |
|---|---|---|
| ነግሠ<br>ሰከወ<br>ኀለየ | መንግሥት<br>መስኮት<br>ማኅሌት | መንግሥት<br>መስኮት<br>ምስጋና |

## <u>፫.፫ የስም ርባታ</u>

ስም የተለያዩ የርባታ ምዕላዶች ያስከትላል፡፡ እነዚህ ምዕላዶች ቁጥርን፣ ፆታንና ሙያን ለማመልከት የምንጠቀምባቸው ናቸው፡፡ ወይም ስሞች ለቁጥር፣ ለፆታና ለሙያ ለሚባሉ ሰዋስዋዊ ባሕርያት ቅርፃቸውን ይቀያይራሉ/ይረባሉ፡፡

### <u>፫.፫.፩ ቁጥር</u>

ቁጥር አንድና ብዙን የምንለይበት የሰዋስው ክፍል ነው፡፡ ስሞች ነጠላና ብዙ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ በግእዝ ቋንቋ ውስጥ በስም ብዜት ላይ ብዙ ለውጦች ይታያል፡፡ ይህም

ይነገርበት ከነበረበት ዘመን የተነሳ እንደ ሆነ ይታመናል፡፡ ይሁን እንጂ ግእዝ ሕግጋቱን ጠብቆ ይበዛል፡፡ ዋና ዋና ሕግጋቱም አፍአዊና ውሳጣዊ ውላጤ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡

### ፫.፫.፩.፩. አፍአዊ ውላጤ

አፍአዊ ውላጤ በቃሉ የሌለ ቀለም ጨምሮ የሚበዛ ነው፡፡ በግእዝ ቋንቋ ነጠላ አንስታይ ፆታን በማመልከት በዋናነት በድኅረ ቅጥያ (ድኅረ ምዕላድ) “ት” ሲሆን ለብዙ ቁጥር “አት”ን ድኅረ ምዕላድ በማስገባት ነው፡፡ ግእዝ “አት” ለብዙ ቁጥር ለተባዕታይና ለአንስታይ ሲጠቀም ይስተዋላል፡፡ ምሳሌ ነቢይ---ነቢያት

የአፍአዊ ውላጤ መደባኛ (ውጫዊ ) አብዥዎች ምዕላድ { “-ት -“አት “አን “-ያት “-ዋት -“ያት እና -“ያን} ሲሆኑ፣ ሁሉም ድኅረ ምዕላዶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ የሚከተለውን ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

| ድኅረ- ምዕላድ | ነጠላ | ብዙ |
|---|---|---|
| -“ት” | መድረሻቸው ራብዕ ድምፅ የሆኑ ስሞችን ያበዛል፡፡ | |
| | ደመና=ደመና<br>ሐዋርያ=ሂያጅ | ደመናት<br>ሐዋርያት |
| --“አት” | መድረሻቸው ሳድስ ድምፅ የሆኑ ስሞችን ያበዛል፡፡ | |
| | ሀብት=ሀብት<br>መስቀል=መስቀል | ሀብት-አት= ሀብታት<br>መሳቅል-አት=መሳቅላት |
| --“አን” | መድረሻቸው ሳድስ ቅጽሎችን ያበዛል፡፡ | |
| | ምሁር=የተማረ<br>ሥዩም=የተሾመ | ምሁራ-አን=ምሁራን<br>ሥዩም-አን=ሥዩማን |
| | መድረሻቸው ኃምስ ድምፅ የሆኑ ስሞችን ያበዛል፡፡ | |
| ያት | ምሳሌ=ምሳሌ<br>ጽጌ=አበባ | ምሳሌያት<br>ጽጌያት |
| --“ዋት” | መድረሻቸው ሳብዕ ድምፅ የሆኑ ስሞችን ያበዛል፡፡ | |
| | ከበሮ=ከበሮ<br>ገቦ=ጎን | ከበሮዋት/ከባርው<br>ገቦዋት |
| -“ያን” | ተባዕታይ ሣልስ ቅጽሎችን ያበዛል፡፡ | |
| | ሐሳዊ=ሀሰተኛ<br>ወላዲ=ወላጅ<br>መራሒ=መሪ<br>ቀታሊ=ገዳይ | ሐሳውያን<br>ወላድያን<br>መራሕያን<br>ቀታልያን |


AbeselomNekatibeb(nabeselom@gmail.com)

## ፫.፫.፩.፪.ውሳጣዊ ውላጤ

ውሳጣዊ ውላጤ ባዕድ ቀለም ሳይጨምር በቃሉ ውስጥ ያሉትን ቀለማት በመለወጥ ብቻ የሚበዛ ነው፡፡ በሌላ በኩል በውሳጣዊ ውላጤ ጊዜ "አ" በመጀመሪያ ሲገባ ውሳጣዊ ውላጤ አድርጎ " ት" ን ይጨምራል፡፡

| አ በመነሻ እየሆነ ውሳጣዊ ውላጤ ሲያደርግ | | ውሳጣዊ ውላጤ እያደረገ "አ" "ት"ን ሲጨመር | | ድኅረ መነሻቸውን በመለወጥ የሚበዙ ቃላት | |
|---|---|---|---|---|---|
| ነጠላ | ብዙ | ነጠላ | ብዙ | ነጠላ | ብዙ |
| ሐመር=መርከብ | አሕማር | ርእስ=ራስ | አርእስት | ከንፈር=ከንፈር | ከናፍር |
| ሌሊት=ሌሊት | ለያልይ | ጥብ=ጡት | አጥባት | መንበር=ወንበር | መናብርት |
| መስኮት=መስኮት | መሳክው | ቤት=ቤት | አብያት | ሰንሰል=ሰንሰለት | ሰናስል |
| ሰሌዳ=ብራና | ሰላድው | ስም=ስም | አስማት | አንበጣ=አንበጣ | አናብጥ |
| ደብር= ተራራ | አድባር | እግዚእ=ጌታ | አጋእዝእት | ሰንበት=ሰንበት | ሰናብት |
| ዶርሆ= ዶሮ | ደዋርህ | በድን= ሬሳ | አብድንት | አንብዕ=እንባ | አናብዕ |
| አድግ=አህያ | አእዱግ | ነምር=ነብር | አናምርት | ገራህት=እርሻ | ገራውህ |
| ፈረስ=ፈረስ | አፍራስ | ጸብእ=ጠብ | አጻብእት | ድንግል=ድንግል | ደናግል |
| ገመል=ግመል | አግማል | ከይሲ=እባብአን | አክይስት | እኅት=እኅት | አኃት |
| ነገር = ነገር | አንጋር | ጼዋ=አይጥ | አናጹት | መቅበርት=መቅበሪያ | መቃብር |

## ፫.፫.፩.፫.የብዙ ብዙ አብኻዎች

| ነጠላ | ብዙ | የብዙ ብዙ |
|---|---|---|
| ሀገር=ሀገር | አህጉር | አህጉራት |
| ሊቅ=የተማረ | ሊቃን | ሊቃውንት |
| ፈለግ=ወንዝ | አፍላግ | አፈላጋት |
| ላህም=ላም | አልህምት | አልህምታት |
| ዘመን=ዘመን፣ወቅት | አዝማን | አዝማናት |
| ሕግ=ሕግ | ሕገግ | ሕግጋት |
| ስነ=ጥርስ | ስነን | አስናን |
| ዕፅ=እንጨት | ዕፀው | ዕፀዋት |
| ዕብን=ድንጋይ | ዕበን | አዕባን |

## ፫.፫.፪. ጾታ

ስሞች ተባዕታይና አንስታይ ተብለው በጾታ ይከፈላሉ፡፡ በሰዋስው ደንብ ወንድና ሴትን እየለየ የሚያስረዳ ሕግ ጾታ ይባላል፡፡ በጾታ ውስጥ ብዙ ቃላት መድረሻቸውን ሲለውጡ ሌሎች ደግሞ ቃል ለዋጭ ናቸው፡፡

### ፩. ቃል ለዋጭ ጾታ

ቃል ለዋጭ ጾታ የሚባሉት በስም ላይ ምንም ዐይነት የጾታ አመልካች ምዕላድ ሳይኖራቸው ተባዕታይንና አንስታይ ጾታን በተለያየ ስም (ቃላት) ሊያመለክቱ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ከዚህ በታች የተገለጹት እንመልከት፡፡

| ተባዕታይ | አንስታይ |
|---|---|
| አብ=አባት | እም=እናት |
| እኁ=ወንድም | እኅት=እኅት |
| ወልድ=ልጅ | ወለት=ሴት ልጅ |
| ቴፌን=ወይፈን | ዕጎልት=ጊደር |
| ገብር= ወንድ አገልጋይ | አመት= ሴት አገልጋይ |
| ምት=ባል | ብእሲት= ሚስት |
| ገመል=ወንድ ግመል | ናቀት=ሴት ግመል |
| ውዕላ= ወንድ ጥንቸል | ወይጠል=ሴት ጥንቸል |

### ፪. መድረሻ ለዋጭ ጾታ

በስሞች ላይ ጾታ አመልካች ምዕላድ በመጨመር የሚገኝ ስም ነው፡፡

| የሚከተሉት ስሞች በመድረሻቸው ላይ "ት"ን በመጨመር አንስታይ ጾታን ያመለክታሉ፡፡ | |
|---|---|
| ብእሲ=ወንድ | ብእሲት=ሴት |
| ነቢይ=ወንድ ነቢይ | ነቢይት=ሴት ነቢይ |
| እግዚእ=ጌታ | እግዝእት/እግዚእት=እመቤት |
| አድግ= ወንድ አህያ | እድግት=ሴት አህያ |
| መርዓዊ=ወንድ ሙሽራ | መርዓት=ሴት ሙሽራ |
| ኢትዮጵያዊ=ኢትዮጵያዊ | ኢትዮጵያዊት=ኢትዮጵያዊት |
| በግዕ=በግ | በግዕት=ሴት በግ |
| ጠሊ=ፍየል | ጠሊት=ሴት ፍየል |

### ፫.፫.፫ . የስም ሙያ

ስሞች በዐረፍተ ነገር ውሰጥ ሦስት ተግባራት አላቸው፡፡ ተግባራቱም ባለቤት፣ ተሳቢና ዘርፍ ሲሆኑ፣ በሰዋስው ሥርዓት የሚገኙበት ሁኔታ ሙያ ተብሎ ይጠራል፡፡

**ለምሳሌ፡-**

| አበበ ሐነጸ ቤተ ትምህርት፡፡ | ሙያ |
|---|---|
| አበበ→ስም | ባለቤት |
| ሐነጸ→ግስ | ማሰሪያ አንቀጽ |
| ቤተ ትምህርት→ስም | ዘርፍ የያዘ ተሳቢ |
| ቤተ→ስም | የሐነጸ ተሳቢ |
| ትምህርት→ ስም | የቤት ዘርፍ |

## ፫.፬ መስተኣምር

መስተኣምር ማለት መታወቂያ፣ የሚታወቅበት፣ አስተዋቂ ማለት ነው፡፡ የተወሰነና ያልተወሰነ መስተኣምር ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡

### ፩. የተወሰነ መስተኣምር

ባለቤቱ ቀድሞ የታወቀ ከሆነ የተወሰነ መስተኣምር ይባላል፡፡ በግእዝ ቋንቋ ዘ (ዘ=ኡ/ው)፡፡ ባለቤቱ ቀድሞ መታወቁን ይጠቁማል፡፡

ምሳሌ፡- ዘመጽአ ዘለኪ መጽሐፍ → መጽሐፉ
ዘኢትዮጵያ ዘዐድዋ እድ → እዱ
ብእሲ-→ብእሲሁ

### ፪. ያልተወሰነ መስተኣምር

ያልተወሰነ መስተኣምር ባለቤቱ አለመታወቁን የሚጠቁም የቋንቋ ሥርዓት ነው፡፡ ሁልጊዜ ከስም ቀድሞ ይገባል፡፡ ያልተወሰነ መስተኣምር በግእዝ በተባዕታይና በአንስታይ ይነገራል፡፡

| ተባዕታይ | አንስታይ |
|---|---|
| አሐዱ-----------------------→አሐደ<br>መጽአ አሐዱ ብእሲ፡፡ (ተገብሮ)<br>ዝኩ አረጋዊ ቀተለ አሐደ ሰብአ፡፡(ገቢር) | አሐቲ-------------------→አሐተ<br>መጽአት አሐቲ ወለት፡፡ (ተገብሮ)<br>ርኢኩ አሐተ ብእሲተ፡፡ (ገቢር) |


AbeselomNekatibeb(nabeselom@gmail.com)

## ፫.፫. ተውላጠ ስም

ተውላጥ ማለት ልዋጭ፣ ምትክ፣ ማለት ነው፡፡ ተውላጠ ስም ተብሎ ሲናበብ ደግሞ የስም ምትክ ማለት ነው፡፡ ተውላጠ ስሞች በሚከተሉት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡

### ፫.፫.፩.ምድብ ተውላጠ ስም

ምድብ ተውላጠ ስሞች በግእዝ ቋንቋ መራሕያን ይባላሉ፡፡ ይህም መርሐ=መራ ከሚለው ግስ የተገኘ ሲሆን ፣ መራሒ=መሪ፣ መራሕያን=መሪዎች ብሎ ይበዛል፡፡ መራሕያን ቁጥራቸው ዐሥር ነው፡፡ እርሱም፡-

| | |
|---|---|
| አነ | ንሕነ |
| አንተ | አንትሙ |
| አንቲ | አንትን |
| ውእቱ | ውእቶሙ |
| ይእቲ | ውእቶን |

መራሕያን ተውላጠ ስም፣ ነባር አንቀጽና አመልካች ቅጽል በመሆን ያገለግላሉ፡፡

#### ፫.፫.፩.፩. መራሕያን (ምድብ ) ተውላጠ ስም ሲሆኑ

መራሕያን በነጠላና በብዙ በሴትና በወንድ በቅርብና በሩቅ ሲከፈሉ ሦስት መደብ ይሆናሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ | ቀዳማይ መደብ (1ኛ መደብ) የወል ፆታ | | |
| | ነጠላ | | ብዙ |
| | ተባዕታይ/ አንስታይ | አነ =እኔ | ንሕነ = እኛ |
| | ካልአይ መደብ ( 2ኛ መደብ ) ቅርብ | | |
| ፪ | ነጠላ | | ብዙ |
| | ተባዕታይ | አንተ = አንተ | አንትሙ=እናንተ |
| | አንስታይ | አንቲ= አንቺ | አንትን =እናንተ |
| | ሣልሳይ መደብ (3ኛ መደብ) ሩቅ | | |
| ፫ | | ነጠላ | ብዙ |
| | ተባዕታይ | ውእቱ = እሱ | ውእቶሙ =እነሱ |
| | አንስታይ | ይእቲ = እሷ | ውእቶን = እነሱ |

**ዐረፍተ ነገር በዐሥሩ መራሕያን**

| | |
|---|---|
| አነ ሖርኩ ኀበ ቤተ ትምህርት | አንትን ሖርክን ኀበ ቤተ ትምህርት |
| አንተ ሖርከ ኀበ ቤተ ትምህርት | ውእቱ ሖረ ኀበ ቤተ ትምህርት |
| አንቲ ሖርኪ ኀበ ቤተ ትምህርት | ይእቲ ሖረት ኀበ ቤተ ትምህርት |
| ንሕነ ሖርነ ኀበ ቤተ ትምህርት | ውእቶሙ ሖሩ ኀበ ቤተ ትምህርት |
| አንትሙ ሖርክሙ ኀበ ቤተ ትምህርት | ውእቶን ሖራ ኀበ ቤተትምህርት |

### ፫.፫.፩.፪. መራሕያን ነባር አንቀጽ ሲሆኑ

መራሕያን ነባር አንቀጽ በመሆን ሲያገለግሉ ፡፡

| መራሕያን | ምሳሌ |
|---|---|
| አነ=ነኝ፣ ነበርሁ፣ ሆንሁ | አነ መምህረ ልሳን አነ፡፡--- እኔ የቋንቋ መምህር ነኝ፡፡ |
| አንተ=ነህ፣ ነበርህ | አንተ መምህረ ልሳን አንተ፡፡--- አንተ የቋንቋ መምህር ነህ፡፡ |
| አንቲ =ነሽ፣ ነበርሽ | አንቲ መምህርተ ልሳን አንቲ፡፡ |
| ንሕነ=ነን፣ ነበርን | ንሕነ መምህራነ ልሳን ንህነ፡፡ |
| ውእቱ =ነው፣ ነበረ፣ ሆነ | ውእቱ መምህረ ልሳን ውእቱ፡፡ |
| ይእቲ=ነች፣ ነበረች | ይእቲ መምህርተ ልሳን ይእቲ፡፡ |
| ውእቶሙ=ናቸው፣ነበሩ | ውእቶሙ መምህራነ ልሳን ውእቶሙ፡፡ |
| አንትሙ=ናችሁ፣ ነበራችሁ | አንትሙ መምህራነ ልሳን አንትሙ፡፡ |
| አንትን=ናችሁ፣ ነበራችሁ | አንትን መምህራተ ልሳን አንትን፡፡ |
| ውእቶን=ናቸው፣ ነበሩ | ውእቶን መምህራተ ልሳን ውእቶን፡፡ |

የውእቱ ባሕርይ ተለዋዋጭ ነው፡፡ውእቱ =ነው፣ ናት፣ ናቸው፣ ነን፣ ናት፣ ናችሁ፣ ነበረች፣ ወዘተ. ምሳሌ፡- ንሕነ ውእቱ ጸሐፍተ ጦማር፡፡ ዳዊት ወአብደላ መምህራን ውእቱ፡፡ አነ ውእቱ ኖላዊ ኄር፡፡ አንቲ ውእቱ ሐዋሪተ ፍኖት፡፡

### ፫.፫.፩.፫. መራሕያን አመልካች ቅጽል ሲሆኑ

መራሕያን አመልካች ቅጽል በመሆን ሲያገለግሉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| አነ = እኔ | አነ መሃሪ | እኔ አስተማሪ ነኝ፡፡ |
| አንተ =አንተ | አንተ መሃሪ | አንተ አስተማሪ ነህ፡፡ |
| አንቲ = አንቺ | አንቲ መሃሪት | አንቺ አስተማሪ ነሽ፡፡ |
| ንሕነ = እኛ | ንሕነ መሃርያን | እኛ አስተማሪዎች ነን፡፡ |
| ውእቱ= ያ | ውእቱ መሃሪ | ያ አስተማሪ ነው፡፡ |
| ይእቲ =ያቺ | ይእቲ መሃሪት | ያች አስተማሪ ነች፡፡ |
| ውእቶሙ = እነዚያ | ውእቶሙ መሃርያን | እነዚያ አስተማሪዎች ነኝ፡፡ |
| አንትሙ=እናንተ | አንትሙ መሃርያን | |
| አንትን=እናንቺ | አንትን መሃርያት | |
| ውእቶን=እነዚያ | ውእቶን መሃርያት | |

## ፫.፮.፪. ባለቤት ተውላጠ ስም

መራሕያን የባለቤት ተውላጠ ስም በመሆን አገልግሎት ሲሰጡ፡፡

<table>
<tr><td rowspan="3">አነ መጻእኩ ኀበ ቤት፡፡<br>አንተ መጻእከ ኀበ ቤት፡፡<br>አንቲ መጻእኪ ኀበ ቤት፡፡<br>ንሕነ መጻእነ ኀበ ቤት፡፡<br>ውእቱ መጻአ ኀበ ቤት፡፡<br>ይእቲ መጻአት ኀበ ቤት፡፡<br>ውእቶሙ መጽኡ ኀበ ቤት፡፡<br>አንትሙ መጻእክሙ ኀበ ቤት፡፡<br>አንትን መጻእክን ኀበ ቤት፡፡<br>ውእቶን መጽአ ኀበ ቤት፡፡</td><td colspan="2"><u>የባለቤት ዝርዝር ቀለማት</u></td></tr>
<tr><td><u>ነጠላ</u></td><td><u>ብዙ</u></td></tr>
<tr><td>አነ→ ኩ<br>አንተ→ከ<br>አንቲ→ኪ<br>ውእቱ→አ፣ኧ፣(ግእዝ)<br>ይእቲ→ት፣አት</td><td>ንሕነ→ነ<br>አንትሙ→ክሙ<br>አንትን→ክን<br>ውእቶሙ→ (ካዕብ)<br>ውእቶን→ኣ፣ (ራብዕ)</td></tr>
</table>

### ምልማድ

**በሚከተሉት ቃላት በአሥሩ መራሕያን ዐረፍተ ነገር ስሩ**

፩. ቆመ ፣ ሖረ ፣ በልዐ ፡፡ ለምሳሌ፡- አነ ሖርኩ መንገለ ባሕር ዳር፡፡

## ፫.፮.፫.ተሳቢ ተውላጠ ስም

ተሳቢ ተውላጠ ስም የግስ ተሳቢ ስም በሌለበት ጊዜ የማሰሪያ አንቀጽ ተሳቢ ሆነው ይነገራሉ፡፡ በሰንጠረዡ ውስጥ የቀረቡትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

| ተሳቢ ተውላጠ ስም | ተሳቢ ስም ሳይኖር ተሳቢ ሲሆኑ | ተሳቢ ስም ሲኖር |
|---|---|---|
| ኪያየ= እኔን<br>ኪያከ = አንተን<br>ኪያኪ =አንቺን<br>ኪያነ= እኛን<br>ኪያሁ= እሱን<br>ኪያሃ = እሷን<br>ኪያክሙ=እናንተን<br>ኪያሆን =እነሱን<br>ኪያክን = እናንተን<br>ኪያሆሙ= እነሱን | ሕግ ያገርር <u>ኪያከ</u>፡፡<br>ሐጎስ ፈነወ <u>ኪያክሙ</u>፡፡<br>ውእቱ ተውክፈ <u>ኪያየ</u>፡፡<br>ጫላ በደረ <u>ኪያክን</u>፡፡<br>ዱጠሮ ፈነወ <u>ኪያኪ</u>፡፡<br>ሐጎስ ፈነወ <u>ኪያሆሙ</u>፡፡<br>ሁሴን ፈነወ <u>ኪያነ</u>፡፡<br>መልካሙ ፈነወ <u>ኪያሃ</u>፡፡ | ዳንኤል ሰበረ <u>ኆኅተ</u><br><br>ጫልቱ ሐነጸት <u>ቤተ</u><br><br>ሐጎስ ፈነወ <u>አግብርተ</u><br><br>ፈይሳ ቀደሰ <u>አልማዝሃ</u><br><br>ጀሚላ ዐደወት <u>ባሕረ</u> |

## ፫.፭.፬. ተጠቃሽ ተውላጠ ስም

| ተጠቃሽ ተውላጠ ስም | ዐረፍተ ነገር | |
|---|---|---|
| ሊተ = ለእኔ፣ የእኔ | ተሐንጸ ቤትየ ሊተ | ሰላም ለከ እኁየ፡፡ |
| ለከ = ለአንተ፣ የአንተ | ተሐንጸ ቤትከ ለከ | ሰላም ለኪ እኅትየ፡፡ |
| ለኪ = ለአንቺ፣ የአንቺ | ተሐንጸ ቤትኪ ለኪ | ሰላም ለክሙ አኃውየ፡፡ |
| ሎቱ = ለእሱ፣ የእሱ | ተሐንጸ ቤትነ ለነ | ሰላም ለክን አኃትየ፡፡ |
| ላቲ= ለእሷ፣ የእሷ | ተሐንጸ ቤቱ ሎቱ | ሰላም ለክሙ አብያጽየ፡፡ |
| ለነ = ለእኛ፣ የእኛ | ተሐንጸ ቤትክሙ ለክሙ | ሰላም ለክሙ አበውየ፡፡ |
| ለክሙ =ለእናንተ፣ የእናንተ | ተሐንጸ ቤታ ላቲ | ሰላም ለኪ እምየ፡፡ |
| ለክን =ለእናንቺ፣ የእናንቺ | ተሐንጸ ቤትክን ለክን | ሰላም ለክሙ አርድእት፡፡ |
| ሎሙ/ሎቶሙ= ለእነሱ፣ የእነሱ | ተሐንጸ ቤቶሙ ሎሙ | ሰላም ለክሙ መምህራነ |
| ሎን/ሎቶን =ለእነሷ፣ የእነሷ | ተሐንጸ ቤቶን ሎን | ኮሌጅ፤ |

### ምልማድ

**የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ወደ ግእዝና አማርኛ ተርጉም፡፡**

፩.ብቻውን ወሰዱት፡፡

፪.ወንድምህ አንተን በጣም ይወድሃል፤

፫. ልጄ መምህርት ናት፡፡

፬. አባታችን እኛን ይወደናል፡፡

፭. አንች ለዳዊት ተስፋው ነሽ፡፡

፮. እናንተን ማን ፈለጋችሁ?

፯. አልማዝ አንችን ተመለከተችሽ፡፡

፰. የሞገስ ልጅ እንቁላል ሰበረች፡፡

፱. ፈረሱ ሎቱ ቀይህ ውእቱ፡፡

፲. ይእቲ ፈነወት ኪያክሙ፡፡

፲፩. ወለታ ለብእሲት ጸላም ይእቲ፡፡

፲፪. ቤትነ ዐቢይ ውእቱ ከመ ቤትክን፡፡

፲፫. አብዲሳ ጸውዐክን ኪያክን፡፡

፲፬. ውእቶን አንስት አክበራ ኪያሆሙ፡፡

፲፭. ሠረገላሁ ለከበደ ትማልም ተገንጸለ፡፡

፲፮. ብሔርክሙ ርኁቅ ውእቱ፡፡

፲፯. አምታቲሆን ሎን ተመይጣ እምቀትል፡፡

፲፰. መኑ ቀተሎን ኪያሆን በሰይፍ፡፡

## ፫.፩.፩. አመልካች ተውላጠ ስም

አመልካች ማለት የአንድን ነገር ወይም አካል ከተናጋሪው መቅረብና መራቅ የሚያመለክት ሰዋስዋዊ ሙያ ሲሆን፣ አመልካች ተውላጠ ስሞች ደግሞ አንድን ነገር ከሚገኝበት ቦታ አንጻር እየጠቀሙ የሚያመለክቱ ቃላት ናቸው፡፡

| ተባዕታይ የቅርብ አመልካች ተውላጠ ስም(አመልካች+ግስ+ ተሳቢ=አመልካች ተወላጠ ስም) | | | |
|---|---|---|---|
| ነጠላ | ትርጉም | ብዙ | ትርጉም |
| አመልካች ተውላጠ ስም | | አመልካች ተውላጠ ስም | |
| ዝ | ይህ፣ ይኸው | እሉ /እሎ | እኒሁ፣ እነዚህ |
| ዝንቱ | ይኸውና፣ ይህ ነው | እሎንቱ | እኒሁና፣ እኒህ |
| ተባዕታይ የሩቅ አመልካች ተውላጠ ስም | | | |
| ነጠላ | ትርጉም | ብዙ | ትርጉም |
| አመልካች ተውላጠ ስም | | አመልካች ተውላጠ ስም | |
| ዝኩ | ያው | ውእቶሙ | እነዚያ |
| ዝክቱ | ያውና | እልኩ | እነዚያው |
| ዝስኩ | ያነው | እልክቱ | እነዚያ ናቸው |
| ውእቱ | ያ | | |
| አንስታይ የቅርብ አመልካች ተውላጠ ስም | | | |
| ነጠላ | ትርጉም | ብዙ | ትርጉም |
| አመልካች ተውላጠ ስም | | አመልካች ተውላጠ ስም | |
| ዛ | ይቺ | እላ | እነዚህ |
| ዛቲ | ይቺው | እሎን | እኒሁ |
| | ይቺውና | እላንቱ | እኒህ ናቸው |
| አንስታይ የሩቅ አመልካች ተውላጠ ስም | | | |
| ነጠላ | ትርጉም | ብዙ | ትርጉም |
| አመልካች ተውላጠ ስም | | አመልካች ተውላጠ ስም | |
| ይእቲ | ያቺ | ውእቶን | እነዚያ |
| እንታክቲ | ያቺው | እልኮን | እነዚያው |
| እንትኩ | ያቺውና | እልክቶን | እነዚያ ናቸው |

አመልካች ተወላጠ ስም ከአመልካች ቅጽል ጋር በንባብ አንድ ናቸው፣ በአገባብ ግን ይለያያሉ፡፡

ሀ. አነ ገበርኩ ግብረ ቤትየ፡፡

ለ. ዝ/ዝንቱ ገብረ ግብረ ቤቱ፡፡

ቀ. እላንቱ ገብራ ግብረ ቤቶን፡፡

በ. እልኮን ገብራ ግብረ ቤቶን፡፡



AbeselomNekatibeb(nabeselom@gmail.com)

ሐ. ዛ/ ዛቲ ገብረት ግብረ ቤታ፡፡
መ. እላ ገብራ ግብረ ቤቶን፡፡
ሠ. እልኩ ገብሩ ግብረ ቤቶሙ፡፡
ሰ. እንታክቲ ገብረት ግብረ ቤታ፡፡
ሸ. ንሕነ ገበርነ ግብረ ቤትነ፡፡
ተ. እሎን ገብራ ግብረ ቤቶን፡፡
ነ. ዝስኩ ገብረ ግብረ ቤቱ፡፡
አ. ውእቱ ቀደሰ ቅዳሴ፡፡
ኀ. ይእቲ ዘመረት ዝማሬ፡፡
ከ. ውእቶሙ ዘመሩ ዝማሬ፡፡

## ፫.፭.፮. <u>መጠይቅ ተውላጠ ስም</u>

መጠይቅ ተውላጠ ስም ጥያቄ ለመጠየቅ የምንጠቀምባቸው ቃላት ናቸው፡፡ በግእዝ መጠይቅ ንኡስ አገባብ ይባላሉ፡፡ ካልተናበቡና የመስተዋድድ ተገዥ ካልሆኑ በቀር በመነሻ ይገባሉ፡፡ መጠይቃን ቃላት እንደሚጠየቀው ነገርና ዐይነት አገባባቸውም ይለያያል፡፡ ይኸውም ለሰው፣ ለነገር፣ ለሁኔታ፣ ለቦታ፣ ወዘተ. ተብለው ይከፈላሉ፡፡

<table>
<tr><td colspan="2">፩. ሰውን ለመጠየቅ የሚያገለግሉ</td><td colspan="2">፪.ነገርን ለመጠየቅ የሚያገለግሉ</td></tr>
<tr><td><u>ነጠላ</u><br>መኑ=ማን<br>አይ=ማን</td><td><u>ብዙ</u><br>እለመኑ=እነማን<br>አያት=እነማን</td><td><u>ነጠላ</u><br>አይ=ምን<br>ምንት= ምንድን<br>ለምንት= ለምን</td><td><u>ብዙ</u><br>አያት=ምኖች<br>ምንታት=ምንድኖች</td></tr>
<tr><td colspan="2">፩. መኑ ውእቱ ዝንቱ ወልድ፡፡<br>፪. ወለተ መኑ አንቲ፡፡<br>፫. ምስለ አይ ተቀትለ ውእቱ በኲናት፡፡</td><td colspan="2">፩. አይ ወድቀ ውስተ ግብ፡፡<br>፪. ምንት ውእቱ ምክሮሙ፡፡<br>፫. በይነ ምንት መጻእከ ቢጽየ፡፡<br>፬.ለምንት ሖርኪ ኀበ ደብረ ብርሃን፡፡</td></tr>
<tr><td colspan="2">፫. ጊዜን ለመጠየቅ የሚያገለግሉ</td><td colspan="2">፬.ቦታን ለመጠየቅ የሚያገለግሉ</td></tr>
<tr><td colspan="2">አይ =መቼ ማእዜ=መቼ</td><td colspan="2">አይ=የት አይቴ=ወዴት</td></tr>
<tr><td colspan="2">፩.ማእዜ ተቀትለ ሐጎስ፧<br>፪.አየ እለተ ተሰቅለ ከበደ፧</td><td colspan="2">፩.እምአይ መጽአ ወልድከ፡፡<br>፪. አይቴ ብሔራ ለጥበብ፡፡</td></tr>
<tr><td colspan="2">፭. ሁኔታንና ድርጊትን ለመጠየቅ የሚያገለግሉ</td><td colspan="2">፭. ቁጥርን ለመጠየቅ የሚያገለግል</td></tr>
<tr><td colspan="2" rowspan="2">እፎ =እንዴት፣ ምን፣ ምንኛ<br>ሁ/ኑ=ን</td><td><u>ነጠላ</u><br>ስፍን=ስንት</td><td><u>ብዙ</u><br>እስፍንት=ምን ያህል</td></tr>
<tr><td colspan="2">፩. እስፍንቱ ውእቱ መዋዕሊሁ፡፡<br>፪. ስፍን ሤጡ፡፡</td></tr>
<tr><td colspan="4"><u>እፎ፣ ሁ፣ ኑ</u> ፡- እፎ በጥያቄ፣ በአንክሮ፣ በድንጋጼ ጊዜ ይነገራል፡፡ ሁ/ኑ፡-በካዕብነት የሚነገሩ የፊደል ቅንጣቶች ናቸው፡፡ በቃላት ትራስ እየሆኑ ጥያቄ ለመጠየቅ ያገለግላሉ፡፡<br>፩. እፎ ውእቱ ብእሲሁ፡፡<br>፪. ንጉሥኑ መጽአ፡፡<br>፫. ተአምርኑ አብያቲሆሙ፡፡<br>፬. አነሁ ውእቱ አባሲ፡፡</td></tr>
</table>

### ፫.፭.፯.፩. አሉታዊ መጠይቅ

ጥያቄን በአሉታ ለማቅረብ አሉታ ነባር አናቀጽን ማለትም አኮ፣ አልቦ፣ ኢ፣ አኮ፣ ሐሰ ከመጠይቃን ፊደላት (ሆሂያት) ሁ/ኑ ጋር በማስገባት መጠቀም ነው፡፡ አኮ፣ አልቦ፣ ኢ፣ አኮ፣ ሐሰ=አይደለም የሚል ፍች ይኖራቸዋል፡፡ ለምሳሌ

| | |
|---|---|
| ፩. አኮኑ ዝንቱ ወልዱ ለጋዲሳ፡፡ | ፭.ኢተመይጠኑ ቢጽነ እምነ ከተማ፡፡ |
| ፪. ኢመጽአኑ አቡከ፡፡ | ፮. አኮሁ ዛቲ ብእሲት እኅትነ፡፡ |
| ፫. ኢሖረትኑ እምኪ ኀበ አዲስ አበባ፡፡ | ፯.አልብከኑ ዘመድ ውስተ ዝንቱ ብሔር፡፡ |
| ፬. አልቦኑ ግብር በቤትክሙ፡፡ | ፰.ኢሖረሁ አቡከ ኀበ ድሬደዋ፡፡ |

**ምልማድ**

**የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ወደ ግእዝና አማርኛ ተርጉም፡፡**

| | |
|---|---|
| ሀ. ይህ ማን ነው? | ቀ. ማእዜ መጽአ ዋቅጅራ፡፡ |
| ለ. ወደማን ተላክህ? | በ. ወልደ መኑ አንተ፡፡ |
| መ. ሀገሩ የት ነው? | ተ. አይ መጽሐፍ፡፡ |
| ሠ. ለምን እዚህ መጣህ? | ነ. ምንት ውእቱ ዝንቱ፡፡ |
| ረ. እድሜህ ስንት ነው? | አ. አንትኑ/ሁ ተዐቢ እምአበበ፡፡ |
| ሰ. አልማዝና አስቴር መቼ መጡ? | ከ. አይቴ ብሔርኪ ሰላማዊት፡፡ |

### ፫.፭.፯.ድርብ ተውላጠ ስም

ድርብ ተውላጠ ስም የምድብ ተውላጠ ስም አባሪ ወይም ደራቢ በመሆን የሚያገለግሉ ቃላት ናቸው፡፡ እነርሱም ከዚህ በታች የተመለከቱት ናቸው፡፡

| ነጠላ | ብዙ |
|---|---|
| ለልየ=እኔ ራሴ | ለሊነ= እኛ ራሳችን |
| ለሊከ=አንተ ራስህ | ለሊክሙ= እናንተ ራሳችሁ |
| ለሊሁ=እሱ ራሱ | ለሊክን=እናንተ ራሳችሁ |
| ለሊኪ=አንች ራስሽ | ለሊሆሙ=እነሱ ራሳቸው |
| ለሊሃ=እሷ ራሷ | ለሊሆን=እነሱ ራሳቸው |

**ለምሳሌ ፡-**

፩. ለልየ ሐነጽኩ ቤተ፡፡-- እኔ ራሴ ቤትን ሠራሁ
፪. ለሊከ ሐነጽከ ቤተ፡፡---አንተ ራስህ ቤትን ሠራህ
፫. ለሊኪ ሐነጽኪ ቤተ፡፡---አንቺ ራስሽ ቤትን ሠራሽ
፬. ለሊሁ ሐነጸ ቤተ፡፡
፭. ለሊሃ ሐነጸት ቤተ፡፡
፮. ለሊነ ሐነጽነ ቤተ፡፡
፯. ለሊክሙ ሐነጽክሙ ቤተ፡፡
፰. ለሊክን ሐነጽክን ቤተ፡፡
፱. ለሊሆሙ ሐነጹ ቤተ፡፡
፲. ለሊሆን ሐነጻ ቤተ፡፡


AbeselomNekatibeb(nabeselom@gmail.com)

## ፫.፭.፰.አገናዛቢ ተውላጠ ስም

አገናዛቢ ማለት አንድን ነገር ከሌላው ጋር የሚያገናዝብ (የሚያያይዝ) ማለት ነው፡፡ የገንዘብንና የግል ንብረትን የሚያመላክቱ አገናዛቢ ተውላጠ ስሞቹ ሦስት ሲሆኑ፣ እነርሱም፡- የ ዘ፣ እንተ፣ እለ፣ ዝርዝሮች ናቸው፡፡

### ፫.፭.፰.፩. የአገናዛቢ ተውላጠ ስም ዝርዝር

| ተባእታይ | ትርጉም | አንስታይ | ትርጉም | የወል | ትርጉም |
|---|---|---|---|---|---|
| ዚኣየ | የኔ፣ የኔው | እንቲኣየ | እኔ፣ የኔይቱ | እሊኣየ | እኔ፣ የኔዎቹ |
| ዚኣከ | ያንተ | እንቲኣከ | ያንተይቱ | እሊኣከ | ያንተዎቹ |
| ዚኣኪ | ያንቺ | እንቲኣኪ | ያንቺይቱ | እሊኣኪ | ያንቺዎቹ |
| ዚኣሃ | የሷ | እንቲኣሃ | የሷይቱ | እሊኣሃ | የሷዎቹ |
| ዚኣነ | የኛ | እንቲኣነ | የኛይቱ | እሊኣነ | የኛዎቹ |
| ዚኣክሙ | የናንተ | እንቲኣክሙ | የናንተይቱ | እሊኣክሙ | የናንተዎቹ |
| ዚኣክን | የናንቺ | እንቲኣክን | የናንቺይቱ | እሊኣክን | የናንቺዎቹ |
| ዚኣሆሙ | የነሱ | እንቲኣሆሙ | የነሱይቱ | እሊኣሆሙ | የነሱዎቹ |
| ዚኣሆን | የነሷ | እንቲኣሆን | የነሷይቱ | እሊኣሆን | የነሷዎቹ |
| ዚኣሁ | የሱ | እንቲኣሁ | የሱይቱ | እሊኣሁ | የሱዎቹ |

ለምሳሌ፡- ፩. ወልደ ዚኣየ አንበበ መጻሕፍቲሁ። -------የኔ ልጅ መጸሐፎቹን አነበበ

፪. ወለተ እንቲኣከ ሠናይት ጥቀ ይእቲ።--------የአንቺ ልጅ በጣም ቆንጆ ናት

**ምልማድ**

የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉም ( ወልጥ ኀበ ልሳነ አምሐራ )፡፡

| | |
|---|---|
| ፩. ወልደ ዚኣየ ዘበጣ ለወለተ ዚኣኪ፡፡ | ፭. ዘዚኣከ ወለት አፍቀረት እኁየ፡፡ |
| ፪. ዐቀበ ዘዚኣየ ምክረ፡፡ | ፮. ርኢኩ ፍጻሜ ዘዚኣሆን፡፡ |
| ፫. አይቴ ሖራ አዋልደ ዚኣክን፡፡ | ፯. ዝኵሉ ዘዚኣየ ውእቱ፡፡ |
| ፬. ውሉደ እሊኣነ መጸኡ ኀቤነ፡፡ | ፰. ብእሲተ እንቲኣከ በከየት በማእከለ ሕዝብ፡፡ |

## ፫.፭.፱.አዛማጅ ተውላጠ ስም

አዛማጅ ማለት አንድን ነገር ከሌላው ጋር የሚያዛምድ ማለት ነው፡፡ አዛማጅ ተውላጠ ስም ተዛማጅ ተውላጠ ስም ተብሎ ይጠራል፡፡ አዛማጅ ተውላጠ ስሞች የሚባሉት ዘ፣ እንተ እና እለ ናቸው፡፡ ለ ን ጨምሮ ዘርፍ አያያዝ ይባላሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

| | |
|---|---|
| ፩. ዘሖረ ይመጽእ፡፡-----የሄደ ይመጣል፡፡ | ፬. ዘበልዐ ባሕቲቶ ይመውት ባሕቲቶ፡፡ |
| ፪. እለ ትነብሩ ተንሥኡ፡፡ | ፭. አንተ ውእቱ ዘብከ ሥልጣን፡፡ |
| ፫. ዘአልቦ ግብር ይትረሳእ አመ ሞተ፡፡ | ፮. ሠናይት ይእቲ እንተ ኀለፈት በቅድሜየ፡፡ |

## ፫.፮.ቅጽል

ቅጽል ቀጸለ=ቀጠለ፣ ጨመረ፣ አቀዳጀ፣ ከሚለው ግስ የወጣ ሲሆን፣ ቅጽል የሚለው ቃል ቅጥያ፣ ተጨማሪ፣ ገላጭ፣ ማለት ነው፡፡ ቅጽል ከዘርና (ውስጠ ዘ፣ መስም፣ ጥሬ ዘር፣ አኀዝ፣ ወገን) ከነባር (ግልጸ ዘ፣ ስመ ተጸውዖ፣ ንኡስና ደቂቅ ቅጽሎች) ይገኛል፡፡ ቅጽል ከባለቤት ቀድሞ ወይም ተከትሎ ይነገራል፤ የስምን ጠባይ ይገልጻል።

### ፫.፮.፩.የቅጽል ዐይነቶች

#### ፫.፮.፩.፩.አመልካች ቅጽል/ደቂቅ ቅጽል

አመልካች ቅጽልና አመልካች ተውላጠ ስም በንባብና በዘር አንድ ናቸው፡፡ ልዩነታቸው በአገባብ ነው፡፡ ስም ሲከተላቸው ቅጽል ይሆናሉ፡፡ ማሰሪያ አንቀጽ ሲከተላቸው ደግሞ ተውላጠ ስም ይሆናሉ፡፡ (አመልካች+ስም+ግስ+ተሳቢ=አመልካች ቅጽል)፡፡

| ለምሳሌ፡- <u>አመልካች ተውላጠ ስም</u> | <u>አመልካች ቅጽል</u> |
|---|---|
| ዝንቱ ውእቱ ወልድየ፡፡ | ዝ ወልድ ኃያል ውእቱ፡፡ |
| ዛቲ ይእቲ ሄለን፡፡ | ዛቲ ወለት እኅትየ ይእቲ፡፡ |

| አመልካች ቅጽል የቅርብ ተባዕታይ ነጠላና ብዙ (ባለቤት) | ተሳቢ (ቅርብ) | ዘርፍ (ቅርብ) | ተቀባይ (ቅርብ) |
|---|---|---|---|
| ነጠላ→ዝ / ዝንቱ<br>ብዙ→እሉ / እሎንቱ | ዘ/ዘንተ<br>እሎንተ/እሉንተ | ዘዝ/ ዘዝንቱ<br>ዘእሉ/ዘእሎንቱ | ለዝ/ ለዝንቱ<br>ለእሉ/ለእሎንቱ |
| <u>የሩቅ ተባዕታይ ነጠላና ብዙ</u><br>ነጠላ→ዝኩ/ ዝስኩ/ ዝክቱ<br>ብዙ→እልኩ/ እልከቱ | <u>ተሳቢ (ሩቅ)</u><br>ዝክተ/ዝኰ/ ዝክቶ<br>እልክተ/ እልኮ | <u>ዘርፍ (ሩቅ)</u><br>ዘዝኩ /ዘዝከቱ<br>ዘእልኩ | <u>ተቀባይ (ሩቅ)</u><br>ለዝኩ/ለዝክቱ<br>ለእልኩ |
| <u>የቅርብ አንስታይ ነጠላና ብዙ</u><br>ነጠላ→ዛ / ዛቲ<br>ብዙ→እላ / እሎን / እላንቱ<br><u>የሩቅ አንስታይ ነጠላና ብዙ</u><br>ነጠላ→እንትኩ / እንታክቲ<br>ብዙ→እልኮን / እልክቶን | <u>ተሳቢ (ሩቅ)</u><br>ዛ/ ዛተ<br>እላንተ<br><u>ተሳቢ (ሩቅ)</u><br>እንታክተ<br>እልክተ | <u>ዘርፍ ( ሩቅ)</u><br>ዘዛ/ ዘዛቲ<br>ዘእላ/ ዘእሎን<br><u>ዘርፍ (ሩቅ)</u><br>ዘእንትኩ/<br>ዘእልክቱ | <u>ተቀባይ (ሩቅ)</u><br>ለዛ/ ለዛቲ<br>ለእላ /ለእሎን<br><u>ተቀባይ (ሩቅ)</u><br>ለእንትኩ<br>ለእልክቱ |

ምሳሌ፡- አመልካች ቅጽልና ሙያቸው ፡፡

| ቅጽል | ስም | ግስ | ተሳቢ |
|---|---|---|---|
| ዝንቱ | ብእሲ | ይገብር | ግብረ |
| ዝስኩ | ወልድ | በልዐ | ኅብስተ |
| እሎንቱ | መምህራን | ይሜህሩ | ጥበበ |
| ዛቲ | ወለት | ተዐቢ | እምአብያጺሃ |
| እንታክቲ | ብእሲት | ጸውዓት | አዋልዲሃ |
| እልኩ | ዕደው | አንከሩ | ምሕረቶ |
| አልኮን | አንስት | ሰትያ | ወይነ |

## ምልማድ

የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገር ወደ አማርኛ ተርጉም፡፡

| | |
|---|---|
| ፩. ዝኩ አረጋዊ አቡየ ውእቱ፡፡ | ፮. ዝንቱ ረድእ አኮ ትጉህ፡፡ |
| ፪. ውእቶን አንስት መጽኣ እምአሰላ፡፡ | ፯. እንታክቲ ብእሲት ጐየት ኀበ ኬንያ፡፡ |
| ፫. እንትኩ መበለት አልባቲ ምጽላል፡፡ | ፰. እሉ ዕደው ይሬእዩ እልክተ አንስተ፡፡ |
| ፬. እላ አንስት ሰከባ ላዕለ አራት፡፡ | ፱. ዝንቱ ብእሲ ቀተለ ዝኰ ከይሲ በበትር፡፡ |
| ፭. ዛቲ ዖፍ ነበረት ላዕለ ዖም ነዊኅ፡፡ | |

## ፫.፯.፩.፭.መጠይቅ ቅጽል

የነገርም ሆነ የዐይነትን ሁኔታ ጠይቀን የምንረዳበት ክፍል መጠይቅ ቅጽል ይባላል፡፡ ለሰውና ለነገር ተብለው ይከፈላሉ፡፡ መጠይቅ ቅጽል ከመጠይቅ ተውላጠ ስም ጋር በንባብ አንድ ሲሆኑ፣ በአገባብ ይለያያሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

| መጠይቅ ተውላጠ ስም | መጠይቅ ቅጽል (የባለቤት ቅጽል) |
|---|---|
| መኑ መጽአ፡፡ | ምንት ግብር ገብረ እኁከ፡፡ |
| አይቴ ሀሎ ዓለሙ፡፡ | አይ ብእሲ ይነብር በደብረ ዳሸን፡፡ |

| ለሰው | | | | ለነገር | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ነጠላ | ተሳቢ | ብዙ | ተሳቢ | ነጠላ | ተሳቢ | ብዙ | ተሳቢ |
| መኑ | መነ | እለመኑ | - | ምንት | ምንተ | ምንታት | ምንታተ |
| አይ | አየ | አያት | አያተ | አይ/ ሚ | አየ | አያት | አያተ |
| ስፍን | ስፍነ | እስፍንት | እስፍንተ | ስፈን | ሰፍነ | እስፍንት | እስፍንተ |
| የዘርፍና የተቀባይን ሙያ ለማግኘት ቃላቱን ሳይለውጡ ዘን ለተሳቢ ለን ደግሞ ለአቀባይ ቃላቱ ላይ መጨመር ነው፡፡ | | | | | | | |

መጠይቅ ቅጽል የባለቤትና የተሳቢ ቅጽል በመሆንያገለግላሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

| የባለቤት ቅጽል | ስም | ግስ | ተሳቢ |
|---|---|---|---|
| አይ<br>መኑ<br>ምንት<br>አይቴ<br>በማእዜ<br>እስፍንቱ | ሰብእ<br>ብእሲ<br>ነገር<br>ሀገር<br>ዕለት<br>መዋዕል | ተማከረ<br>ሖረ<br>መጽአ<br>ይከውን<br>ይትመየጥ<br>ኀለፉ | ምስሌሁ<br>ኀበ ፀባይ<br>ህየ<br>ምዕራፈ<br>ኀበ ቤቱ<br>- |

ምልማድ

የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ወደ ግእዝ ተርጉም፡፡

፩. ማን ጥበበኛ ይህን ይሰራል?

፪. ስንት ዘመናት አለፉ?

፫. ይህ ሰው ማን ነው?

፬. የአስተማራችሁ መምህር ማን ነው?

፭. በቀለ ለምን ሄደ?

፮. ቶማስ መቼ መጣ?

፯. ሰሎሜ ምን ሆነች?

፰. ከሱ ጋር ማን ሰው ሔደ?

፱. ዳዊት ማንን ሰው ገደለ?

፲. የዓለሙ አገር የት ነው?

## ፫.፮.፩.፯.አዛማጂ ቅጽል (ግልጸ ዘ )

አዛማጅ ቅጽሎች (ግልጸ ዘ ቅጽል) በግስ ላይ እየወደቁ የአንቀጽ ማሰሪያነትን በማስቀረት ለስሞች የሚቀጸሉ ናቸው፤ወይም ስሞችን የሚገልጹ ናቸው፡፡ እነርሱም፡- ዘ፣ እንተ እና እለ ሲሆኑ፣ ከአጠገባቸው ስም ከሌለ አዛማጅ ተውላጠ ስም ይሆናሉ፡፡

ግለጸ ዘ

| | |
|---|---|
| ፩. ብእሲ ዘጸሐፈ ጦማረ ፡፡ | ፮. ሳሙኤል ዘቀተሎ መስፍን፡፡ |
| ፪. ሣራ እንተ በከየት ኢረከበት ውሉዳ፡፡ | ፯. አንስት እለ የአምራ ፈቲለ፡፡ |
| ፫. አስቴር እንተ ኖመት ላዕለ አራት፡፡ | ፰. አርድእት እለ የአምሩ ጥበበ፡፡ |
| ፬. ብእሲ ዘመጽአ ትማልም አርከየ ፡፡ | ፱. አበበች እንተ ታስቴደሉ ምግበ ለደቂቃ፡፡ |
| ፭. አበው እለሞቱ በእንተ ፍቅረ ሀገሮሙ፡፡ | |

ዘ፣ እንተ፣ እለ፣ በመካከል ሲገቡ ዘርፍ አያያዝ ሲባሉ በመጀመሪያ ሲገቡ ዘርፍ ደፊ ይባላሉ፡፡ ዘ፣ እንተ፣ እለ እና ለ አራቱ ሆሄያት (ግእዝ፣ ኃምስ፣ ራብዕ፣ ሳብዕ) ባለቤትን ሲያይዙ ሲያናብቡ /የ/ ተብለው በቅጽል መንገድ ይተረጎማሉ፡፡


AbeselomNekatibeb(nabeselom@gmail.com)

**ለምሳሌ፡-**

| ዘርፍ አያያዝ | ዘርፍ ደፊ | ተናባቢ | ተጠቃሽ |
|---|---|---|---|
| መዝሙር ዘዳዊት<br>መጻሕፍት እለ አበበ<br>ብእሲት እንተ ከበደ | ዘዳዊት መዝሙር<br>እለ አበበ መጻሕፍት<br>እንተ ከበደ ብእሲት | መዝሙረ ዳዊት<br>መጻሕፍተ አበበ<br>ብእሲተ ከበደ | መዝሙሩ ለዳዊት<br>መጻሕፍቲሁ ለአበበ<br>ብእሲቱ ለከበደ |

<u>ዘ</u> በሰዋስወ ግእዝ ውስጥ የተለያዩ አገልግሎት አሉት(<u>ቅጽል፣ መስተኣምር ወዘተ. </u>)፡፡

## <u>፫.፯.፩.፰.የቅጽል ተነጻጻሪ</u>

አንዱን ከሌላው የምናነጻጽርበት ወይም የምናወዳድርበት ክፍል የቅጽል ተነጻጻሪ ይባላል፡፡ ይህም አነጻጻሪ፣ አብላጭ እና አበላላጭ ተብሎ በሦስት ይከፈላል፡፡

| አነጻጻሪ | አብላጭ | አበላላጭ | |
|---|---|---|---|
| ከመ=እንደ | እም=ከ<br>እምነ=ከ | እምኵሉ=ከሁሉም<br>እምኵሎሙ= ከሁሉም | ጥቀ=በጣም<br>ፈድፋደ=እጅግ በጣም |
| ምሳሌያት፣ | | | የቅጽል ዐይነት |
| ፩. አበበ መምህር ውእቱ ከመ ገመቹ፡፡ | | | አነጻጻሪ |
| ፩. ወልድየ የዐቢ እምነ ወልድከ፡፡<br>፪. አንተ ትንእስ እምኔሁ፡፡<br>፫. አነ አፈቅር አቡየ እምነ እምየ፡፡ | | | አብላጭ |
| ፩. ዝንቱ ነጋዲ ባዕል ውእቱ እምኵሎሙ ነጋድያነ ድሬደዋ፡፡<br>፪. ዝ መምህር ክቡር ጥቀ እምኵሎሙ መምህራን፡፡<br>፫. አብዱከሪም ኄር እምኵልነ፡፡<br>፬. ዝስኩ መርድእ ፍቁር ውእቱ ፈድፋደ በኀበ ሕዝብ እምኵሎሙ አርድእት፤ | | | አበላላጭ |

## ፫.፮.፩.፱. ውስጠ ዘ ቅጽል

ውስጠ ዘ ቅጽል (ዘ፣ እንተ፣ እለ) የተባሉት ዐበይት አገባባት ሳይገቡበት በትርጉም /የ/ የሚል ትርጉም የሚያመጣልን ቃል ነው፡፡ ለምሳሌ፣

| ግለጸ-ዘ | ውስጠ-ዘ | |
|---|---|---|
| ፩. አንበሳ ዘጸግበ ሥጋ | ገባሪ=የሚሰራ | ብእሲ ገባሪ |
| ፪. አንስት እለ ሞታ በእንተ ፍቅረ ከርሣን | ቅዱስ=የተመሰገነ | ብእሲ ቅዱስ |
| ፫. ብእሲት እንተ ሖረት ኀበ ብሔራ | ቀታሊ=የሚገድል | አበበ ቀታሊ |

ውስጠ ዘ ቅጽል ሳድስና ሣልስ ውስጠ ዘ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ እነዚህ ቅጽሎች ውስጣዊና ውጫዊ ቅጥያዎችን በመጨመር ሊበዙ ይችላሉ፡፡

| ሀ. ሣልስ ውሰጠ ዘ | ለ. ሳድስ ወስጠ ዘ |
|---|---|
| ጸሓፊ =ጸሓፊ<br>ዘፋኒ=ዘፋኝ<br>ሰማዒ= ሰሚ | ኅሩይ=ምርጥ<br>ምሁር=የተማረ<br>ሥዩም= የተሾመ |
| ምሳሌ፡-ጸሓፊ ሐነስ ጸሐፈ መልእክተ፡፡<br>ዘፋኒት አስቴር ዘፈነት ሎቱ፡፡ | ትጉህ ብእሲ መጽአ ኀቤነ፡፡<br>ዝንቱ ውእቱ ጥዑም ዓሣ፡፡ |

**ሐ. መድብል፡-** የተባዕታይንና የአንስታይን ብዙ ቁጥር አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡

| | |
|---|---|
| መገበ→መገብት | ጸሐፊ→ጸሐፍት |
| ጠበ→ጠበብት | ቀተለ→ቀተልት |
| ሰረቀ→ሰረቅት | ነግሡ→ ነገሥት |

### መ. መስም ውስጠ ዘ (ባዕድ) ቅጽል

መስም ቅጽል ባዕድ ቅጽል ተብሎ ይጠራል፤ ከመደበኛ አንቀጽ የሌለ ባዕድ ቀለም "መ" መነሻ አድርጎ የሚነገር ስም ነው፡፡

<table>
<tr><td>ግስ መስም</td><td>ምሳሌ፡-</td><td colspan="2">ሰያፍ ቅጽል፡-ከመስም ጋር የሚመሳሰል ባዕድ ፊደል የማይጨምር ቃል ነው፡፡</td></tr>
<tr><td>ዘመረ-→ መዘምር<br>መሀረ → መምህር<br>ገብረ→ መስተገብር</td><td>ከበደ መዘምር<br>ኪሮስ መምህር<br>አብደላ መስተገብር</td><td>ዐብየ→ዐቢይ<br>ሐደሰ→ ሐዲስ</td><td>ዐቢይ→ ዐቢያን<br>ዐባይ→ ዐባያት</td></tr>
</table>

## ፫.፯.አኃዝ

አኃዝ ማለት መጀመሪያ፣ ጥንት ማለት ነው፡፡ አኃዝ ለመላው ቁጥር ሁሉ ጠቅላይ ስም ነው፡፡ ከባለቤት እየገባ የመብዛትንና የማነስን ትርጉም ይገልጻል፡፡ አኃዝ መደበኛ፣ ሕገኛ፣ ክፍላዊ፣ ዕጽፋዊ፣ መድበላዊ ቁጥር ተብሎ ሊከፈል ይችላል፡፡

### ፫.፯.፩. መደበኛ

መደበኛ ቁጥር የተበታተኑትን ነገሮች ሰብስቦ የሚያሳይ የጅምላ ቁጥር ነው፡፡ የአጻጻፍ ሥርዓቱም በአኃዝና በፊደል ሲሆን ፣ በተባዕታይና በአንስታይ ፆታ ይነገራል፡፡

| ተባዕታይ | | አንስታይ | ፳=ዕሥራ | 20 |
|---|---|---|---|---|
| ፩=አሐዱ | 1 | አሐቲ | ፴=ሠላሳ | 30 |
| ፪=ክልኤቱ | 2 | ክልኤቲ | ፵=አርባ | 40 |
| ፫=ሠለስቱ | 3 | ሠላስ | ፶=ሃምሳ | 50 |
| ፬=አርባዕቱ | 4 | አርባዕ/ራብዕ | ፷=ስሳ/ስድሳ | 60 |
| ፭=ኀምስቱ | 5 | ኀምስ | ፸=ሰብዓ | 70 |
| ፮=ስድስቱ | 6 | ስሱ | ፹=ሰማንያ | 80 |
| ፯=ሰብአቱ | 7 | ሰብዑ | ፺= ተስዓ | 90 |
| ፰=ስምንቱ | 8 | ሰማኒ | ፻=ምእት | 100 |
| ፱=ተሰዐቱ | 9 | ተስዑ | ፳፻=ዕሥራ ምዕት | 2000 |
| ፲=ዐሠርቱ | 10 | ዐሥሩ | ፼=እልፍ | 10000 |
| ፲ወ፩=ዐሠርቱ ወአሐዱ | 11 | ዐሥር ወአሐቲ. | ፲፼=ዐሠርቱ እልፍ | 100000 |
| ፲ወ፪=ዐሠርቱ ወክልኤቱ- | 12 | ዐሥር ወክልኤቲ | | |
| ፲ወ፫=ዐሠርቱ ወሠለስቱ. | 13 | ዐሥር ወሠላስ | | |
| ፲ወ፬=ዐሠርቱ ወአርባዕቱ | 14 | ዐሥር ወአርባዕ | በፆታ ሲታይ፣ | |
| ፲ወ፭=ዐሠርቱ ወአምስቱ | 15 | ዐሥር ወኃምስ | ፻=ምእት ዕደው | |
| ፲ወ፮=ዐሠርቱ ወስድስቱ | 16 | ዐሥር ወስሱ | ፻=ምእት አንስት | |
| ፲ወ፯=ዐሠርቱ ወሰብአቱ | 17 | ዐሥር ወሰብዑ | ዐሥር ወአሐቲ አንስት መጽኣ | |
| ፲ወ፰=ዐሠርቱ ወስምንቱ | 18 | ዐሥር ወሰሙኑ | | |
| ፲ወ፱=ዐሠርቱ ወተሰአቱ | 19 | ዐሥር ወተስዑ | ዕሥራ ወክልኤቲ አንስት ሖራ | |

ለምሳሌ፡- ፩. ክልኤቱ ዕደው ዐርጉ ሐመረ፡፡

፪. ሠለስቱ ደቂቅ ተወደዩ ውስተ ግብ፡፡

## ፫.፯.፪.ሕገኛ

ሕገኛ ቁጥር ደረጃን የሚያሳይ ቀጥር ሲሆን በተባዕታይና በአንስታይ ፆታ ይነገራል፡፡ ሕገኛ ቁጥር የሚነሳው በራብዕ ፊደል/ሆሄ ነው፡፡ ሕገኛ ቁጥር (ዊ፣ ት፣ ዪ፣ ይ) ምዕላድ ጨምሮ ይነገራል፡፡

| ተባዕታይ | | አንስታይ | |
|---|---|---|---|
| ፩ዊ=ኣሐድ፣ቀዳሚ.........ቀዳማይ/ዊ--- | 1ኛ | ፩ዊት=ኣሐቲ፣ቀዳሚት.....ቀዳማዊት/ይት | 1ኛ |
| ፪ዊ=ካልእ....................ካልኣይ/ዊ -- | 2ኛ | ፪ዊት=ካልእት...............ካልኣዊት/ይት | 2ኛ |
| ፪ዊ=ዳግም..................ዳግማይ/ዊ -- | 2ኛ | ፪ዊት=ዳግሚት............ዳግማዊት/ይት | 2ኛ |
| ፫ዊ=ሣልስ ..................ሣልሳዊ/ይ - | 3ኛ | ፫ዊት=ሣልስት ............ሣልሳዪት/ዊት | 3ኛ |
| ፬ዊ=ራብዕ.................. ራብዓይ/ዊ-- | 4ኛ | ፬ዊት=ራብዕት.............ራብዓዊት/ይት | 4ኛ |
| ፭ዊ=ኃምስ................ ኃምሳይ/ዊ---- | 5ኛ | ፭ዊት=ኃምስት.............ኃምሳዊት/ይት | 5ኛ |
| ፮ዊ=ሳድስ..................... ሳድሳዊ/ይ-- | 6ኛ | ፮ዊት=ሳድስት............ ሳድሳይት/ዊት | 6ኛ |
| ፯ዊ=ሳብዕ...................ሳብኣዊ/ይ---- | 7ኛ | ፯ዊት=ሳብዕት.............ሳብኣይት/ዊት | 7ኛ |
| ፰ዊ=ሳምን..................ሳምናይ/ዊ---- | 8ኛ | ፰ዊት=ሳምንት.............ሳምናዊት/ይት | 8ኛ |
| ፱ዊ=ታስዕ..................ታስዓዊ/ይ---- | 9ኛ | ፱ዊት=ታስዕት............ታስዓይት/ዊት | 9ኛ |
| ፲ዊ=ዓሥር..................ዓሥራዊ/ይ--- | 10ኛ | ፲ዊት=ዓሥርት............ዓሥራይት/ዊት | 10ኛ |
| ፳ዊ (ዕሥራዊ)......................... | 20ኛ | ፳ዊት = (ዕሥራዊት).........ዕሥራይት | 20ኛ |
| ፴ዊ.......................................... | 30ኛ | ፴ዊት.................................... | 30ኛ |
| ፵ዊ.......................................... | 40ኛ | ፵ዊት.................................... | 40ኛ |
| ፶ዊ.......................................... | 50ኛ | ፶ዊት.................................... | 50ኛ |
| ፷ዊ.......................................... | 60ኛ | ፷ዊት.................................... | 60ኛ |
| ፸ዊ.......................................... | 70ኛ | ፸ዊት.................................... | 70ኛ |
| ፹ዊ.......................................... | 80ኛ | ፹ዊት................................. | 80ኛ |
| ፺ዊ.......................................... | 90ኛ | ፺ዊት.................................... | 90ኛ |

## ፫.፰.ግስ

ግስ ገሰ፣ ዳበሰ፣ ያዘ ካለው ሥርወ ቃል የወጣ ሲሆን፣ ግስ ማለት የቃላት መራቢያ፣ መሰብሰቢያ፣ ገስጋሽ፣ ተመላላሽ፣ ተወራራሽ፣ ማለት ነው፡፡ አንድም የቋንቋ ጓዝ፣ የዘርና የነባር እክት ማለት ነው፡፡ ግስ ድርጊት መደረጉን ሁኔታ መሆኑን የሚያሰረዳ ቃል ነው፡፡ በአጠቃላይ ግስ ሁለት ባሕርያት አሉት፡፡ እነርሱም፡- የዐረፍተ ነገር ማሰርያ መሆንና በውስጡ የተለያዩ ቅጥያዎችን መያዝ ነው፡፡ ግስ በይዘቱ ርባ ቅምር፣ ነጠላ ግስ (አንቀጽ) እና ርባ ግስ ተብሎ በሦስት ክፍሎች ሊከፈል ይችላል፡፡

## ፫.፰.፩.አርእስተ ግስ

የግስ አርእስት ማለት የግስ አለቆች ማለት ነው፡፡ የግስ አርእስት የምንላቸው የጊዜን ግብር የሚመሩ በርባታቸውና በሰዋስዋዊ አገባባቸው ለጠቅላላው ግስ መሪዎች ሆነው በእነሱ የአረባብ ዘዴ ሌሎች እነርሱን መሰል ግሶች እነርሱን (የግስ አርእስትን) መሠረት በማድረግ የሚረቡ መሆናቸውን የሚለዩልን ግሶች ናቸው፡፡ የታወቁት የግስ አርእስት ስምንት ወይም ሰባት ሲሆኑ፣ የየራሳቸው መለያ ፊደል አላቸው፡፡ በተናጠል ቤት ይባላሉ፡፡ በተጨማሪም የራሳቸው ሡራዊት አላቸው፡፡

**የግስ አርእስት**

፩. ቀተለ = ገደለ
፪. ማህረከ=ማረከ
፫. ቀደሰ =አመሰገነ፣ አከበረ፣ ለየ
፬. ተንበለ=ለመነ፣ ማለደ
፭. ባረከ = ባረከ፣ መረቀ፣ አመሰገነ
፮. ብህለ =አለ
፯. ዴገነ =ተከተለ
፰. ጦመረ= ደብዳቤ ጻፈ

**ምሳሌ፡-**

| | |
|---|---|
| ፩. ውእቱ ቀተለ አንበሳ፡፡ | ፭. ወሬዛ ባረከ አዝማዲሁ፡፡ |
| ፪. ዓለሙ ቀደሰ ከበደሀ ትማልም ፡፡ | ፮. ይእቲ ጦመረት ጦማረ ለአቡሃ፡፡ |
| ፫. ዳንኤል ማህረከ ዘንተ፡፡ | ፯. ውእቱ ዴገነ አኃዊሁ ፡፡ |
| ፬. ውእቱ ተንበለ በእንተ ወልዱ፡፡ | ፰. አነ እመጽእ ጌሠመ ብህለ ፊይሳ፡፡ |

## ፫.፰.፫.ርባ ግስ

የግእዝ ግሶች ርባታቸውን የሚጀምሩት በሦስተኛ መደብ በቀዳማይ አንቀጽ ነው፡፡ የትንቢት እና የአሁን ጊዜ በግእዝ አንድ ዓይነት የግስ አወራረድ አላቸው፡፡ ዘንድ አንቀጽና ትእዛዝ አንቀጽም አንድ ዓይነት ናቸው፡፡ በተጨማሪም ግስ ሲገሰስ ለቀዳማይ ግስ መነሻ የነበረው ቀለም በካልኣይ ጊዜ ይነሳል የካልኣይ ቅድመ መድረሻ ደግሞ ይጠብቃል፡፡ ይህ ሕግ የሚጸናው (ሀ ፣ ኀ፣ ሐ፣ አ፣ ዐ) ፊደላት ያልገቡበት ግስ ሲሆን ነው፡፡ በርባታ ጊዜ የመድረሻ ፊደሎች ሳድስ መሆናቸው ካልኣይና ትእዛዝን ያመለክታሉ፡፡ ግስ ከታች በተገለጸው የአረባብ ስልት ይረባል፡፡

## ፫.፰.፫.፩. የግስ ርባታ አወራረድ

### የቀተለና የቀደሰ ግስ ርባታ

| ፩. ቀተለ | ትርጉም | ሙ.ያ | ፪.ቀደሰ | ትርጉም | ሙ.ያ |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀተለ | ገደለ | ኀ.አንቀጽ | ቀደሰ | አመሰገነ | ኀ.አንቀጽ |
| ይቀትል | ይገድላል | ትን.አንቀጽ | ይቄድስ | ያመስግን | ትን.አንቀጽ |
| ይቅትል | ይገድል | ዘ.አንቀጽ | ይቀድስ | ያመሰግን ዘንድ | ዘ.አንቀጽ |
| ይቅትል | ይገድል | ትእ.አንቀጽ | ይቀድስ | ያመስግን | ትእ.አንቀጽ |
| ቀቲል/ቀቲሎት | መግደል | አርእስት | ቀድሶ/ቀድሶት | ማመስገን | አርእስት |
| ቀታሊ | የገደለ | ሣ.ው.ዘ | ቀዳሲ | ያመሰገነ | ሣ.ው.ዘ |
| ቀታልያን | የገደሉ | ሣ.ው.ዘ.ተ | ቀዳስያን | ያመሰገኑ | ሣ.ው.ዘ.ተ |
| ቀታሊት | የገደለች | ሣ.ው.ዘ.አ | ቀዳሲት | ያመሰገነች | ሣ.ው.ዘ.አ |
| ቀታልያት | የገደሉ | ሣ.ው.ዘ.አ | ቀዳስያት | ያመሰገኑ/ሴቶች | ሣ.ው.ዘ.አ |
| ቅቱል | የተገደለ | ሳ.ው.ዘ.ተ | ቅዱስ | ምስጉን | ሳ.ው.ዘ.ተ |
| ቅቱላን | የተገደሉ | ሣ.ው.ዘ.ተ. | ቅዱሳን | ምስጉኖች | ሣ.ው.ዘ.ተ |
| ቀታሊ | ገዳይ | ስም | ቅድስት | የተመሰገነች | አን.ቅጽል |
| ቀቲሎ | ገድሎ | ቦዝ አንቀጽ | ቀዳሲ | አመስጋኝ | ስም |
| ቀትል | ውጊያ | ዘ. ዘርእ | ቀዲሶ | አመስግኖ | ቦዝ አንቀጽ |
| ቅትለት | አገዳደል | ሳቢ ዘርእ | ቅዳሴ | ምስጋና | ጥሬ ዘርእ |
| መቅትል | መግደያ/መሳ | መስም | መቅደስ | ማመስገኛ | መስም |
| ምቅታል | መግደያ/ቦታ | ባዕድ ዘርእ | ቅድሳት | ክብር፣መሥዋዕት | ምዕ. ዘርእ |

### የማህረከና የተንበለ ግስ ርባታ

| ፫.ማህረከ | ትርጉም | ሙ.ያ | ፬. ተንበለ | ትርጉም | ሙ.ያ |
|---|---|---|---|---|---|
| ማህረከ | ማረከ | ኀ.አንቀጽ | ተንበለ | ለመነ | ኀ.አንቀጽ |
| ይማህርክ | ይማርካል | ትን.አንቀጽ | ይተነብል | ይለምናል | ትን.አንቀጽ |
| ይማህርክ | ይማርካል | ዘ.አንቀጽ | ይተንብል | ይለምን | ዘ.አንቀጽ |
| ይማህርክ | ይማርክ | ትእ.አንቀጽ | ይተንብል | ዘንድ | ትእ.አንቀጽ |
| ማህርኮ/ማህርኮት | መማረክ | አርእስት | ተንብሎ/ተንብሎት | ይለምን | አርእስት |
| ማህራኪ | የሚማርክ | ሣ.ው.ዘ | ተንባሊ | መለምን | ሣ.ው.ዘ |
| ማህራክያን | የሚማርኩ | ሣ.ው.ዘ.ተ | ተንባሊት | ለማኝ | ሣ.ው.ዘ.አ |
| ማህራኪት | የምትማርክ | ሣ.ው.ዘ.አ | መተንብል | የምትለምን | ሣ.ው.ዘ.ተ |
| ማህራክያት | የሚማርኩ | ሣ.ው.ዘ.አ | መተንብልት | የሚያላምን | ሣ.ው.ዘ.አ |
| ምህሩክ | የተማረከ | ሳ.ው.ዘ.ተ | ተንቢሎ | የምታላመን | ቦዝ አንቀጽ |
| ማህራኪ | ማራኪ | ሣ.ው.ዘ.ተ | ተንባል | ለመኖ | ሳ.ውስጠ ዘ |
| ምህርካ | ምርኮ | ጥሬ ዘርእ | ተንባላት | አማላጂ | ሳድስ ቅጽል |
| | | | ትንባሌ | አማላጆች | ጥሬ ዘርእ |
| | | | | ልመና | |

## የባረከና የዴገነ ግስ ርባታ

| ፳. ባረከ | ትርጉም | ሙያ | ፲. ዴገነ | ትርጉም | ሙያ |
|---|---|---|---|---|---|
| ባረከ | ባረከ | ኀ.አንቀጽ | ዴገነ | ተከተለ | ኀ.አንቀጽ |
| ይባርክ | ይባርካል | ትን.አንቀጽ | ይዴግን | ይከተላል | ትን.አንቀጽ |
| ይባርክ | ይባርክ ዘንድ | ዘ.አንቀጽ/ | ይዴግን | ይከተል ዘንድ | ዘ.አንቀጽ/ |
| ይባርክ | ይባርክ | ትእ.አንቀጽ | ይዴግን | ይከተል | ትእ.አንቀጽ |
| ባርኮ/ባርኮት | መባረክ | አርእስት | ዴግኖ/ዴግኖት | መከተል | አርእስት |
| ባራኪ | የባረከ | ሣ.ው.ዘ | ዴጋኒ | ተከታይ | ሣ.ውስጠ ዘ |
| ባራክያን | የባረኩ | ሣ.ው.ዘ.ተ | ዴጋንያን | የሚከተሉ | ሣ.ው.ዘ.ተ |
| ባራኪት | የባረከች | ሣ.ው.ዘ.አ | ዴጋኒት | የምትከተል | ሣ.ው.ዘ.አ |
| ባራክያት | የተባረኩ/ለሴቶች | ሣ.ው.ዘ.አ | ዴጋኒያት | የሚከተሉ | ሣ.ው.ዘ.አ |
| ቡሩክ | የተባረከ | ሳ.ው.ዘ.ተ | ዴጊኖ | ተከትሎ | ቦዝ አንቀጽ |
| ባራኪ | የሚባርክ | ሣ.ው.ዘ.ተ | ዴጋን | ቀስት | ዘመድ ዘርእ |
| ባሪኮ | ባርኮ | ቦዝ አንቀጽ | | | |
| ቡራኬ | ቡራኬ | ጥሬ ዘርእ | | | |
| በረከት | በረከት | ሳቢ ዘርእ | | | |

## የብህለና የጦመረ ግስ ርባታ

| ፲. ብህለ | ትርጉም | ሙያ | ፹. ጦመረ | ትርጉም | ሙያ |
|---|---|---|---|---|---|
| ብህለ | አለ | ኀ.አንቀጽ | ጦመረ | ደብዳቤ ጻፈ | ኀ.አንቀጽ |
| ይብል | ይላል | ትን.አንቀጽ | ይጦምር | ደብዳቤ ይጽፋል | ትን.አንቀጽ |
| ይብሀል | ይል ዘንድ | ዘ.አንቀጽ/ | ይጦምር | ደብዳቤ ይጽፋል | ዘ.አንቀጽ/ |
| ይብሀል | ይበል | ትእ.አንቀጽ | ይጦምር | ደብዳቤ ይጻፍ | ትእ.አንቀጽ |
| ብሂል/ብሂሎት | ማለት | አርእስት | ጦምሮ/ጦምሮት | ደብዳቤ መጻፍ | አርእስት |
| ባሃሊ | ያለ | ሣ.ው.ዘ | ጦማሪ | ደብዳቤ የሚጽፍ | ሣ.ው.ዘ |
| ባሃልያን | ያሉ | ሣ.ው.ዘ.ተ | ጦማርያን | ደብዳቤ የሚጽፉ | ሣ.ው.ዘ.ተ |
| ባሃሊት | ያለች | ሣ.ው.ዘ.አ | ጦማሪት | ደብዳቤ የምትጽፍ | ሣ.ው.ዘ.አ |
| ባህልያት | ያሉ | ሣ.ው.ዘ.አ | ጦማርያት | ደብዳቤ የሚጽፉ | ሣ.ው.ዘ.አ |
| ብሁል | የተባለ | ሳ.ው.ዘ. | ጦማር | ደብዳቤ | ዘመድ ዘርእ |
| ብሂሎ | ብሎ | ቦዝ አንቀጽ | ጦሚሮ | ደብዳቤ ጽፎ | ቦዝ አ. |
| ባሃሊ | የሚል | ስም | | | |
| ባህል | አባባል | ዘመድ ዘርእ | | | |

## ፫.፰.፫.፪.የግስ ርባታ በዐሥሩ መራሕያን

በርባታ ጊዜ ከቀዳማይ አንቀጽ ቀጥሎ በካልኣይ በዘንድና በትእዛዝ አንቀጽ በመነሻ ላይ (በቅድመ መነሻ ላይ) የሚገኙ ቀለማት ይገኛሉ፡፡ በግእዝ ሰዋስው አሥራወ ትንቢት ይባላሉ "የአንቀጽ ሥሮች" ማለት ነው፡፡ ቀለማቱም (ይ፣ እ፣ ት፣ ን) ሲሆኑ፣ ከትንቢት በላይ አይወጡም ከትእዛዝ በላይ አይወርዱም፡፡[2] በትንቢት፣ በዘንድ፣ በትእዛዝ ይነገራሉ፡፡ ነገር ግን ትእዛዝ አንቀጽ በአራቱ ቅርቦች(አንተ፣ አንቲ፣ አንትሙ፣ አንትን) ብቻ ያለአሥራው ይገሰሳል፡፡ ለምሳሌ፡- የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| | |
|---|---|
| <u>፩ኛ መደብ ነጠላ</u> | <u>፩ኛ መደብ ነጠላ ብዙ</u> |
| አነ ቀተልኩ = እኔ ገደልኩ | ንሕነ ቀተልነ = ገደልን |
| አነ እቀትል = እኔ እገድላለሁ | ንሕነ ንቀትል = እንገድላለን |
| አነ እቅትል =እገድል ዘንድ/ ዘንድ አንቀጽ/ | ንሕነ ንቅትል = እንገድል ዘንድ |
| አነ እቅትል = ልግደል / ትእዛዝ/ | ንሕነ ንቅትል = እንግደል |
| <u>በገብረ ቤት</u> | <u>፪ኛ መደብ አንስታይ ነጠላ</u> |
| <u>፪ኛ መደብ ተባዕታይ ነጠላ</u> | አንቲ ገበርኪ = ሠራሽ |
| አንተ ገበርከ = አንተ ሠራህ | አንቲ ትገብሪ = ትሠሪያለሽ |
| አንተ ትገብር = አንተ ትሠራለህ | አንቲ ትግበሪ = ትሠሪ ዘንድ |
| አንተ ትግበር = አንተ ትሠራ ዘንድ | አንቲ ግበሪ =ሥሪ |
| አንተ ግበር = አንተ ሥራ | |

### ፪. በቀደሰ ቤት

| | |
|---|---|
| <u>፫ኛ መደብ ተባዕታይ ነጠላ</u> | <u>፫ኛ መደብ አንስታይ ነጠላ</u> |
| ውእቱ ቀደሰ = አመሰገነ | ይእቲ ቀደሰት = አመሰገነች |
| ውእቱ ይቄድስ =ያመሰግናል | ይእቲ ትቄድስ =ታመሰግናለች |
| ውእቱ ይቀድስ = ያመሰግን ዘንድ | ይእቲ ትቀድስ =ታመሰግን ዘንድ |
| ውእቱ ይቀድስ =ያመስግን | ይእቲ ትቀድስ =ታመስግን |
| <u>፪ኛ መደብ ተባዕታይ ብዙ</u> | <u>፪ኛ መደብ አንስታይ ብዙ</u> |
| አንትሙ ቀተልክሙ =ገደላችሁ | አንትን ቀተልክን =ገደላችሁ |
| አንትሙ ትቀትሉ =ትገድላላችሁ | አንትን ትቀትላ =ትገድላላችሁ |
| አንትሙ ትቅትሉ =ትገድሉ ዘንድ | አንትን ትቅትላ =ትገድሉ ዘንድ |
| አንትሙ ቅትሉ = ግደሉ | አንትን ቅትላ =ግደሉ |

[2] አሥራው መሠረታቸው ሳድስ ሲሆን ነገር ግን /ሀ/አ/ መነሻ ባላቸው ግሶች ግእዝና ራብዕ ይሆናሉ፡፡ እንዲሁም /ወ/ና/የ/ ያለበት ግስም በ /ወ/ እና /የ/ ዐመል ምክንያት መሠረታቸውን ይለቃሉ፡፡

| ፫ኛ መደብ ተባዕታይ ነጠላ | ፫ኛ መደብ አንስታይ ነጠላ |
|---|---|
| ውእቶሙ ቀተሉ =ገደሉ<br>ውእቶሙ ይቀትሉ =ይገድላሉ<br>ውእቶሙ ይቅትሉ =ይገድሉ ዘንድ<br>ውእቶሙ ይቅትሉ =ይገድሉ | ውእቶን ቀተላ =ገደሉ<br>ውእቶን ይቀትላ = ይገድላሉ<br>ውእቶን ይቅትላ = ይገድሉ ዘንድ<br>ውእቶን ይቅትላ = ይግደሉ |

## ፫.፰.፬.የግስ ዐይነቶች

የግእዝ ግሶች በዐይነታቸው (በተግባራቸው) ተሻጋሪና (ገቢር)፣ ኢተሻጋሪ (ተገብሮ) ግሶች ተብለው በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

### ፫.፰.፬.፩. ተሻጋሪ (ገቢር) ግሶች

ተሻጋሪ ግሶች ተሳቢነት ያላቸው ሲሆኑ ድርጊት ወደ ተደራጊ መሻገሩን የሚያሳዩ የግስ ዐይነቶች ናቸው፡፡ ብዙውን ቦታ ይዘው የሚገኙት እነዚህ ግሶች ናቸው፡፡ እነዚህ ግሶች ተሻጋሪ (ገቢር) እንዲሁም "ተ" ን ባዕድ ፊደል ቅድመ ምዕላድ በማስገባት ኢተሻጋሪ (ተገብሮ) ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ከታች በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን እንመልከት፡፡

| ተሻጋሪ (ገቢር) ሲሆኑ | ኢተሻጋሪ (ተገብሮ) ሲሆኑ |
|---|---|
| ቀተለ=ገደለ<br>በልዐ=በላ<br>ጸሐፈ=ጻፈ<br>ገብረ=ሠራ<br>ሰብሐ=አመሰገነ<br>ሠርዐ= ሰራ | ተቀትለ =ተገደለ<br>ተበልዐ =ተበላ<br>ተጽሕፈ= ተጻፈ<br>ተገብረ =ተሰራ<br>ተሰብሐ=ተመሰገነ<br>ተሠርዐ=ተሰራ |

### ፫.፰.፬.፪.ኢተሻጋሪ ግሶች

ኢተሻጋሪ ግሶች የመሳብ ባሕርይ የሌላቸው ግሶች ሲሆኑ፣ ድርጊቱ በአድራጊ ላይ ተወስኖ መቅረቱን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡-ቆመ፣ ሞተ፣ ወረደ፣ ሐይወ፣ መጽአ፣ ዐርገ፣ ነደ፣ ሐጸ፣ ወዘተ. እነዚህ ግሶች ሕጹጸ ባዕድ ተገብሮ ይባላሉ።

- ሐይወ ከበደ፡፡     መጽአ አቡየ፡፡
- ነደ እሳት፡፡     ሐጸ ማይ፡፡


AbeselomNekatibeb(nabeselom@gmail.com)

## ምልማድ

**ወልጥ ኀበ ልሳነ አምሐራ፡፡**

፩. ለብሰ ልብሶ ወሖረ ኀበ ቤተ ትምህርት፡፡
፪. በልዐት ጀሚላ ኅብስተ፡፡
፫. አንፈራጳ አንስት አመ ረከባ አዝማዲሆን፡፡
፬. አንተኑ መምህረ ልሳን ወሚመ እኁከ፡፡
፭. ብዙኃን ሕዝብ አንቃእደዉ ኀበ ሰማይ፡፡
፮. ከበደ ሜጠ መጻሕፍትየ ዘወሰዶሙ፡፡
፯. ለመኑ ጸሐፍከ ዘንተ ጦማረ፡፡
፰. ፀር በርበረ ቤትየ ወቀተለ ከልብየ፡፡
፱. ለምንት ሤጥከ ልብሰከ፡፡
፲. ይእቲ ወለት ነጸረት ኀበ ቤታ፡፡
፲፩. መኑ ነበበ ዘንተ፡፡
፲፪. ገብረ ፈጣሪ ብርሃናተ፡፡
፲፫. ተንበለ ዓለሙ ፈጣሪሁ፡፡
፲፬. ባረከ ጫላ ሐጎስሀ፡፡
፲፭. ያደ ሳሙኤል ኀበ አርባ ምንጭ፡፡
፲፮. መሐመድ ቦአ ኀበ ቤቱ፡፡

## ፫.፰.፭.አዕማደ ግስ

አዕማድ የዐምድ ብዙ ቁጥር ሲሆን ዐምድ ዐመደ=ቀረጠ፣ ደገፈ፣ ጸና፣ ከሚለው ግስ የወጣ ቃል ነው፡፡ አዕማደ ግስ ማለት የግስ ምሰሶዎች /ደጋፊዎች/ እንደ ማለት ነው፡፡ አዕማድ በቋንቋ ሥርዓት ውስጥ ትልቅ ድረሻ ያላቸው የጊዜን፣ የድርጊትን፣ አፈጻጸም የሚያሳዩ አናቅጽ ናቸው፡፡ ተ-፣ አ-፣ አስተ-፣ አን- እና አስ- የተባሉትን ባዕዳን ፊደላት በግስ መደበኛ ዘር ላይ በመነሻ እየጨመሩ ይነገራሉ ፡፡ የተለመዱት የአዕማድ ዐይነቶች አድራጊ፣ አስደራጊ፣ ተደራጊ ፣ ተደራራጊ፣ አደራራጊ ሲሆኑ፣ ከዚህም በላይ ሊሰፉ ይችላሉ፡፡

| ዐምድ | ግስ | ትርጉም |
|---|---|---|
| አድራጊ | ቀተለ | ገደለ |
| አስደራጊ | አቅተለ (የአድራጊ አስደራጊ ነው) | አስገደለ (እንዲገድል አደረገ) |
| ተደራጊ | ተቀትለ | ተገደለ |
| ተደራራጊ | ተቃተለ | ተገዳደለ |
| አደራራጊ | አስተቃተለ | አገዳደለ/አጋደለ |

## ምልማድ

**የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች ወደ አማርኛ ተርጉም፡፡**

| | |
|---|---|
| ፩. አበበ ቀተለ አንበሳ፡፡ | ፬. ተቀትለ ብእሲ በኲናት፡፡ |
| ፪. አበበ አቅተለ ሐጎስሃ፡፡ | ፭. ተቃተሉ ዕደው ምስለ አንስት፡፡ |
| ፫. አስተቃተለ ከበደ አልማዝሃ ምስለ መልካሙ፡፡ | ፮. አስተቅተለ ሁሴን ለጀሚላ በነፍጥ፡፡ |

## ፫.፰.፮.ኢሕጋውያን ግሶች

ኢሕጋውያን ግሶች በስም፣ በቅጽል፣ በግስ ርባታ ጊዜ ዘመድ ሆሄያትን በመዋጥ (በመተው) የሚነበቡና የሚጻፉ ሲሆኑ፣ በተጨማሪም ልዩ ልዩ ዐመልን ያለቤታቸው በመውረስና ባዕድ ፊደላትን በመጨመር የሚታወቁ ናቸው። ኢሕጋውያን ግሶች የሚባሉት /አ/ እና /ሀ/ ያሉበት ግስ፣ /ወ/ እና /የ/ የሚገኙበት ግስ (የግስ ዐመል የሚታይባቸው ፩. ሀ፣ ኀ፣ ሐ፣ ዐ፣ አ ፪. ወ ፣ የ) እና ደጊመ ድምፅ ያሉባቸው ግሶች ሲሆኑ፣ "ይቤ"ም ከኢሕጋውያን ግሶች ይመደባል፡፡

፪. የ "ወ" እና የ "የ" ዐመል፡- የ "ወ" እና የ "የ" ዐመል መጉረድና ድምፅ መለወጥ ነው፡፡ ራሳቸውን እያጠፉ ለሌሎች ድምፆች መወልጣነ ድምፅ ( /ወ/ ካእብና ሳብእ ማድረግ /የ/ ሣልስና ሳብዕ ማድረግ ነው) ይሆናሉ፡፡

**"ወ"**

የ"ወ" አመል በ"ቀተለ" ቤት በካልኣይ፣ በዘንድና በትእዛዝ አንቀጽ ራሱን ይጎርዳል፡፡ ደጊመ(ድምፅ) ሆሄ ከሆነ ግን አይጎርድም፡፡ ለምሳሌ፡- ከወወ= ቀለጠፈ፡፡

ቀዳማይ አንቀጽ→ወረደ=ወረደ ደወየ=ታመመ ተለወ=ተከተለ ከወወ=ቀለጠፈ

ካልአይ አንቀጽ→ ይወረድ ይደዊ ይተሉ ይከውው

ሣልሳይ አንቀጽ→ ይረድ ይድወይ ይትሉ ይክውው

"ወ" በቀደሰ የግስ መድረሻ ሲሆን በካልኣይና በትእዛዝ አንቀጽ እራሱን ይጎርዳል፡፡ ለምሳሌ፡- ዘመወ= አመነዘረ

ቀዳማይ አንቀጽ→ ዘመወ.......................................................ቀደሰ

ካልአይ አንቀጽ →ይዜሙ.......................................................ይቄድስ

ሣልሳይ አንቀጽ→ ይዘሙ.......................................................ይቀድስ

በተጨማሪም "ወ" መድረሻ ሲሆን ካልኣዩ ሳድሱን ጎርዶ ካዕብና ሳብዕ ያደርጋል (ምሳሌ፡- ዘረወ=በተነ በገቢር-ግስ ዘረወ---ቀዳማይ፣ ይዘሩ---ካልኣይ፣ በተገብሮ-ግስ ተዘርወ---ቀዳማይ ይዘሮ----ካልአይ)፡፡

**"የ"**

የ"የ" ዐመል መጉረድና ሣልስ ማድረግ ነው፡፡ በቀተለ ቤት በግስ መሀል ሲሆን፣ መነሻው ሊሆን የሚችለውን ራሱን ጎርዶ ኀምስ ያደርጋል (ሠየጠ--ወደ ሤጠ ይለወጣል)፡፡

በተጨማሪም "የ" በቀተለ ቤት በቀዳማይ ሲገኝ በካልኣይ በሣልሳይ ወዘተ. ራሱን ይጎርዳል፡፡ ለምሳሌ፡- "የ" በቀተለ ቤት፣ ጸገየ=አበበ፡፡ "የ" በቀደሰ ቤት፣ የበበ=እልል አለ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ቀዳማይ አንቀጽ→ | ጸገየ..............ቀተለ | የበበ..............ቀደሰ |
| ካልአይ አንቀጽ→ | ይጸጊ............ይቀትል | ይዬብብ.........ይቄድስ |
| ሣልሳይ አንቀጽ→ | ይጽጊ............ይቅትል | ይየብብ..........ይቀድስ |

**ሀ. ደጊመ ድምፅ ፡-** ደጊመ ድምፅ ያለው የሦስት እግር ግሶች በቀተለ ቤት እንደ /ወ/ እና /የ/ ይጎርዳሉ፡፡ ነገር ግን እንደ /የ/ እና /ወ/ ሦስተኛውን ፊደል ጎርዶ ሳብና ካዕብ ወይም ሣልስ ማድረግ ሳይሆን እየጠበቁ የሁለት እግር ግሶች መሆን ነው፡፡ ለምሳሌ፡-

- ጠቢብ→ጠበ ነዲድ→ነደ
- ነቢብ→ነበ ወዘተ.

ደጊመ ድምፅ ያላቸውና ባለሦስት እግር ግሶች ሆነው የማይጎርዱ ቃላት ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ሐተተ፣ ኀሠሠ፣ ሣረረ፣ መነነ ወዘተ. ፡፡ እንዲሁም ገብሰሰ፣ ደምሰሰ፣ ደንገገ ወዘተ. የመሳሰሉት ባለ አራት ፊደል ግሶች ይገኛሉ፡፡

**ለ. ወኀጥያን ፊደላት (ጎራጅ ፊደላት)፡-** ወኀጥያን ፊደላት አራት ናቸው፡፡ እነርሱም፡- (ቀ፣ ከ፣ ገ፣ ነ) ናቸው፡፡ በግስ መድረሻ ላይ ጠብቀው እየተነገሩ በአምስቱ ቅርቦች የሚነገረውን አቅራቢውን "ከ" ድምፅን ውጦ ማስቀረት ነው፡፡ ምሳሌ፡-አጥመቀ=አጠመቀ፣ ሰበከ=ሰበከ፣ ኀደገ=ተወ ፣ኮነ=ሆነ ፡፡ ይህም በምዕራፍ ሁለት በሥርዓተ ንባብ ውስጥ ተገልጿል፡፡

**ሐ. ይቤ=አለ፡-** ይቤ ለየት ያለ፣ በቀዳማይና በካልኣይ የራሱ አካሄድ ያለው ኢ.ሕጋዊ ግስ ነው፡፡ ይቤ ለየት ያለበት ምክንያት የሚጀምረው በሳድስ ሲሆን፣ የሚጨርሰው ደግሞ በኃምስ ስለሆነ ነው፡፡

**፩. የይቤ ርባታ**

ይቤ → ቀዳማይ አንቀጽ
ይብል → ካልአይ አንቀጽ
ይበል → ሣልሳይ አንቀጽ
ይበል → ትእዛዝ አንቀጽ

**፪. በዐሥሩ መራሕያን ሲዘረዘር**

| | |
|---|---|
| ውእቱ ይቤ = አለ | ንሕነ ንቤ= አልን |
| አነ እቤ= አልሁ | አንትሙ ትቤሉ=አላችሁ |
| አንተ ትቤ= አልህ | አንትን ትቤላ=አላችሁ |
| አንቲ ትቤሊ= አልሽ | ውእቶሙ ይቤሉ= አሉ |
| ይእቲ ትቤ= አለች | ውእቶን ይቤላ= አሉ |

**ምሳሌ፡-**

ይቤ መጽሐፍ "ኢትቅናእ ላዕለ እኩያን"::
ይቤለኒ አርክየ "ተመየጥ ኀበ ግብርከ"::
ይቤሎ አበበ ለቢጹ "አይቴ ነበርከ"
ትቤላ እም ለወለታ "ብልዒ ድራረኪ"::

## ፫.፰.፰. ነባር አንቀጽ

ነባር አንቀጽ ማለት ሳይለወጥ የኖረ፣ ነዋሪ አንቀጽ ማለት ሲሆን፣ ከቀዳማይ በቀር ካልኣይ ሣልሳይ የሌለው ብቸኛ የሆነ የግስ ክፍል ነው፡፡ ነባር አንቀጽ ጽድቅ(አዎንታ)ና አሉታ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡

### ፫.፰.፰.፩.አዎንታ (ጽድቅ) ነባር አንቀጽ፡-

በጽድቅ የሚነገሩ ነባር አንቀጾች ውእቱ፣ (ቦ እና ሎ) ናቸው፡፡ በተጨማሪም እወ እና ኦሆ ከአዎንታ ነባር አንቀጽ ይመደባሉ፡፡

፩. ውእቱ፡- መደበኛ አንቀጽ ሆኖ በቅርብና በሩቅ በተባዕታይና በአንስታይ በነጠላና በብዙ እየረባ በመሆንና በመኖር ግስ ይተረጎማል፡፡ ውእቱ ለቀሪዎቹ ተውላጠ ስሞች መሠረት በመሆኑ ዘጠኙም እርሱን መስለው በመኖርና በመሆን ግስ ይረባሉ፣ ይተረጎማሉ፡፡

| ውእቱ የመሆን ግስ ሲሆን | ውእቱ የመኖር ግስ ሲሆን |
|---|---|
| ውእቱ = ነው፣ ኾነ<br>ይእቲ = ናት፣ ኾነች<br>አንተ= ነህ፣ ኾንህ | ውእቱ = አለ፣ ነበረ፣ ኖረ<br>ይእቲ = አለች፣ ነበረች፣ ኖረች<br>አንተ= አለህ፣ ነበረህ፣ ኖርህ |
| ለምሳሌ፡-መኑ ይእቲ እምየ፡፡<br>አነ ውእቱ ኅብስተ ሕይወት፡፡<br>አንተ ውእቱ መርድእ፡፡ | ለምሳሌ፡- አንትሙ ጼው ለምድር፡፡<br>ንሕነሰ አግብሪትከ ንሕነ፡፡ |

፪. ቦ፡- በመሆን እና በመኖር ግስ ስልት እየረባ በዐሥሩ መራሕያን ይነገራል፡፡

ሀ. ቦ በመሆን ግስ ስልት ሳይዘረዝር ይወርዳል፡፡ ቦ አነ= እኔ አለሁ፣ ኖርሁ፣ ኖሬያለሁ፣ ነበርሁ ፡፡ ቦ ንሕነ= እኛ አለን፣ ኖርን፣ ኖረናል፣ ነበርን ወዘተ. ፡፡ ለምሳሌ፡-

| | |
|---|---|
| ቦ አነ በውስተ ቤተ ተውኔት፡፡ | በቴያትር ቤት ውስጥ ነበርሁ:: |
| ቦ ንሕነ በውስተ ቤተ ተውኔት፡፡ | በቴያትር ቤት ውስጥ ነበርን:: |
| ቦ አንተ በውስተ ቤተ ተውኔት፡፡ | በቴያትር ቤት ውስጥ ነበርህ:: |
| ቦ አንቲ በውስተ ቤተ ተውኔት፡፡ | በቴያትር ቤት ውስጥ ነበርሽ:: |
| ቦ አንትሙ በውስተ ቤተ ተውኔት፡፡ | በቴያትር ቤት ውስጥ ነበራችሁ:: |
| ቦ አንትን በውስተ ቤተ ተውኔት፡፡ | በቴያትር ቤት ውስጥ ነበራችሁ:: |
| ቦ ውእቱ በውስተ ቤተ ተውኔት፡፡ | በቴያትር ቤት ውስጥ ነበረ:: |
| ቦ ይእቲ በውስተ ቤተ ተውኔት፡፡ | በቴያትር ቤት ውስጥ ነበረች:: |
| ቦ ውእቶሙ በውስተ ቤተ ተውኔት፡፡ | በቴያትር ቤት ውስጥ ነበሩ:: |
| ቦ ውእቶን በውስተ ቤተ ተውኔት፡፡ | በቴያትር ቤት ውስጥ ነበሩ:: |

ለ. ቦ በመኖር ግስ ስልት ዘርዝሮ በብትን ዐመል እየረባ እስከ ዐሥር መደብ ይነገራል፡፡ ይህም የአንድን ነገር (አካል) በባለቤቱ መያዙን የሚያመለክት ግስ የመኖር ግስ ይባላል፡፡ የቦ ዝርዝር በዓሥሩ መራሕያን ከዚህ በታች ተገልጿል፡፡

| | |
|---|---|
| ብየ= በእኔ አለብኝ፣ አለኝ፣ ነበረኝ<br>ብከ=በአንተ አለብህ፣ አለህ፣ ነበረህ<br>ብኪ=በአንቺ አለብሽ፣ አለሽ፣ ነበረሽ<br>ቦ/ቦቱ=በእሱ አለበት፣ አለው፣ ነበረው<br>ብነ=በእኛ አለብን፣ አለን፣ ነበረን | ብክሙ= በእናንተ አለባችሁ፣ አላችሁ<br>ቦን= በእኔ አለብኝ፣ አለኝ፣ ነበረኝ<br>ብክን=በእናንተ አለባችሁ፣ አላችሁ ቦሙ=በእነሱ አለባቸው፣ አላቸው፣ ነበራቸው<br>ባ/ባቲ= በእሷ አለባት፣ አላት፣ ነበራት |
| ምሳሌ፡- አለው<br>ብየ መጽሐፍ=መጽሐፍ አለኝ፡፡<br>ብኪ መጽሐፍ= መጽሐፍ አለሽ፡፡<br>ብከ መጽሐፍ=መጽሐፍ አለህ፡፡<br>ባ/ባቲ መጽሐፍ=መጽሐፍ አላት፡፡<br>ቦ/ቦቱ መጽሐፍ=መጽሐፍ አለው፡፡ | ብክሙ መጽሐፍ=መጽሐፍ አላችሁ፡፡<br>ብክን መጽሐፍ=መጽሐፍ አላችሁ፡፡<br>ቦሙ መጽሐፍ=መጽሐፍ አላቸው፡፡<br>ቦን መጽሐፍ=መጽሐፍ አላቸው፡፡<br>ብነ መጽሐፍ=መጽሐፍ አለን፡፡ |

ሐ. ሎ፡- መስተዋድድ (ደቂቅ አገባብ) ነው፡፡ ሙያው ምስጢር አቀባይ ነው፡፡ በዐሥሩ መደብ በጥሬ ዘርእ አመል ይዘረዝራል፡፡ ይህም የሚከተለው ነው፡፡

| ነጠላ | | ብዙ | |
|---|---|---|---|
| ልየ/ሊተ<br>ለኪ<br>ለከ | ሎ/ ሎቱ<br>ላ/ላቲ | ለክሙ<br>ለክን<br>ለነ | ሎሙ<br>ሎን |

/ለ/አገባብነቱን ሳይለቅ ዘርዝሮ በመኖር ግስ ስልት ይተረጎማል፡፡ ይህም እንደሚከተለው ነው፡፡

| | |
|---|---|
| ሎ/ ሎቱ=አለው፣ ነበረው፣ አለለት፣ ይገባል<br>ላ/ላቲ=አላት፣ ነበራት፣ አለላት፣ ይገባል<br>ሎሙ=አላቸው፣ ነበራቸው፣አለላቸው፣ ይገባል<br>ሎን=አላቸው፣ ነበራቸው፣ አለላቸው፣ ይገባል<br>ለኪ=አለሽ፣ ነበረሽ፣ አለልሽ፣ ይገባል | ለከ=አለህ፣ ነበረህ፣ አለልህ፣ ነበረልህ፣ ይገባል<br>ለክሙ=አላችሁ፣ነበራችሁ፣ አለላችሁ፣ ይገባል<br>ለክን=አላችሁ፣ ነበራችሁ፣ አለላችሁ፣ ይገባል<br>ልየ/ሊተ=አለኝ፣ ነበረኝ፣ አለለት፣ ይገባል<br>ለነ=አለን፣ ነበረን፣ አለልኝ፣ ነበረልኝ፣ ይገባል |

<u>ምሳሌ፡-</u>

| | |
|---|---|
| ሰላም ሊተ/ልየ =ሰላም ለእኔ ይሁን፡፡<br>ሰላም ለኪ=ሰላም ለአንቺ ይሁን፡፡<br>ሰላም ለከ=ሰላም ለአንተ ይሁን፡፡<br>ሰላም ለክሙ=ሰላም ለእናንተ ይሁን፡፡<br>ሰላም ለክን=ሰላም ለእናንተ ይሁን፡፡ | ሰላም ሎሙ= ሰላም ለእነሱ ይሁን፡፡<br>ሰላም ላቲ= ሰላም ለእሷ ይሁን፡፡<br>ሰላም ሎቱ= ሰላም ለእሱ ይሁን፡፡<br>ሰላም ለነ=ሰላም ለእኛ ይሁን፡፡<br>ሰላም ሎን=ሰላም ለእነሱ ይሁን፡፡ |
| <u>ምሳሌ፡-</u><br>ለከ ስብሐት = ምስጋና ለአንተ ይሁን፡፡<br>ለኪ ስብሐት= ምስጋና ለአንቺ ይሁን፡፡<br>ለክሙ ስብሐት= ምስጋና ለእናንተ ይሁን፤ | ለክን ስብሐት= ምስጋና ለእናንተ ይሁን፤<br>ሎሙ ሕግ ወሎሙ ሥርዓት=ሥርዓትና ሕግ አላቸው፡፡ |

<u>፫. እወ እና ኦሆ፡-</u>በአዎንታ የሚነገሩ ነባር አናቅጽ ናቸው፡፡ እወ=አዎ፣ እውነት፣ በእውነት፣ ተብሎ ይተረጎማል፡፡ ኦሆ ማለት ደግሞ እሺ ማለት ነው፡፡ ተቃራኒያቸው እንዳዒና እንቢ ሲሆኑ፣ እንቢ በዐሥሩ መራሕያን ይዘረዝራል፡፡ እንዳዒ ደግሞ በለ ይዘረዝራል፡፡ እንዳዒ ሎቱ፣ ላቲ፣ ሎሙ፣ ወዘተ. እያለ ይጓዛል፡፡

## ፫.፰.፰.፪. <u>አሉታ ነባር አንቀጽ</u>

በአሉታ የሚነገሩት ነባር አናቅጽ አኮ፣ ሐሰ እና ኢ፣ ናቸው፡፡ በተጨማሪም አልቦ ከሰዋስው በፊት ወይም በኋላ እየገባ የቦ አሉታ ተቃራኒ ሆኖ አለመኖርን በመግለጽ የሚነገር ነባር አንቀጽ ነው፡፡ አኮ እና ኢ አይደለም፣ አልሆነም፣ የለም፣ አልኖረም፣ አልነበረም፣ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡

<u>ምሳሌ፡-</u>አኮ

| | |
|---|---|
| አኮ አርድእት ንሕነ | አኮ ዝንቱ ግእዛንነ |
| አኮ ሕያዋን ውእቶሙ | አኮ ሒጣን ቃልየ |
| አኮ ሓጺር ሳምሶን | አኮ አበበ ፀርየ አላ ፍቁርየ |

አኮ /ሁ/ እና /ኑ/ ን ይዞ ሲነገር ጥያቄ ይሆናል፡፡

፪. ኢ፡-/ኢ/ ለምሳሌ፡-

| | |
|---|---|
| ኢተመየጠ አቡየ እምዘሐረ . --- አባቴ ከሔደበት አልተመለሰም<br>ዘሐሙም ብእሲ ኢበልዐ እክለ ወኢሰትየ --- የታመመው ሰው እህል አልበላም፤ አልጠጣም<br>ኢታንሥእ ዘኢያንበርከ፡፡<br>ኢገብረ =አልሠራም<br>ኢይገብር = አይሠራም | ኢይግበር =እንዳይሠራ<br>ኢይግበር = አይሥራ<br>ኢገቢሮ = ሳይሠራ |

በተጨማሪም በኀላፊ /አል/ በትንቢትና በትእዛዝ /አ/ በዘንድ/ እንደ፣ ላ፣ ሳ፣/ በቦዝ /ሳ/ ተብሎ ይተረጎማል፡፡ እንደ ሐሰ እና አኮ ኢቦቱ፣ ኢሎቱ፣ ወዘተ. እያለ በዐሥሩ መራሕያን ይዘረዝራል በማለት ያስረዳሉ፡፡

፫. ሐሰ፡- ሐሰ በአሉታነት የሚነገር ነባር አንቀጽ ሲሆን፣ ከሐሰወ የተከፈለ ነው። "ሐሰ"ን ነባር ያሰኘው "ወ" ን በመጉረዱና ኢሕጋዊ በመሆኑ ነው። ሐሰ =ሐሰት፣ አይደለም፣ አይሆንም፣ አይሁን፣ አይገባም፣ ወዘተ. ። ሲዘረዝም እንደ ሚከተለው ነው።

፫.፩. ሐሰ ቦ/ቦቱ፡- ሐሰ በ "ቦ" ተዘርዝሮ ሲወርድ እንደሚከተለው ነው፡፡

ሐሰ ብየ= አይሁንብኝ፣ አይድረስብኝ፣ ሕልም ይሁንልኝ

ሐሰ ብከ= አይሁንብህ፣ አይድረስብህ፣ ሕልም ይሁንልህ

ሐሰ ብኪ= አይሁንብሽ፣ አይድረስብሽ፣ ሕልም ይሁንልሽ

ወዘተ.

፫.፪. ሐሰ ሎ/ ሎቱ፡- ሐሰ በ/ሎ/ ሲዘረዘር የሚከተለውን ትርጉም ይሰጣል፡፡

ሐሰ ሎ/ ሎቱ= አይሁንለት፣ ሐሰት ይሁንለት

ሐሰ ላ/ላቲ= አይሁንላት፣ ሐሰት ይሁንላት

ሐሰ ሎሙ= አይሁንላቸው፣ ሐሰት ይሁንላቸው

ሐሰ ሎን= አይሁንላቸው፣ ሐሰት ይሁንላቸው

ወዘተ.

፬. አልቦ፡- አልቦ የ/ቦ/ አፍራሽ ነው፡፡ ትርጉሙም የለም፣ አልነበረም ማለት ነው፡፡ ከቦ ውጭ በሌላ ቃል አይገባም፡፡ በዐሥሩ መራሕያን ይዘረዝራል፡፡

ለምሳሌ ፡- ሀ. አልቦ ዘመድ በጊዜ መከራ . --- በመከራ ጊዜ ዘመድ የለም፡፡

ለ. አልብየ ዘመድ ዘእንበለ ፈጣሪ --- ያለ ፈጣሪ ዘመድ የለኝም፡፡

ሐ. ለእሉ ነዳያን አልቦሙ ዘመድ --- ለነዚያ ድሆች ዘመድ የላቸውም፡፡

መ. አልባቲ ውሉድ ለዛቲ ብእሲት--- ለዚች ሴት ልጆች የሏትም፡፡



AbeselomNekatibeb(nabeselom@gmail.com)

## ፫.፱.ተውሳከ ግስ

ተውሳከ ግስ ማለትም የግስ ተጨማሪ፣ የግስ ረዳት ማለት ነው፡፡ ቅጽል ስምን እንደሚያጎላምስ ተውሳከ ግስም ከግስ አጠገብ እየዋለ ግስን ያጐላምሳል፡፡ በአጠቃላይ ተውሳከ ግስ ከግስ ላይ እየተጨመረ የግሱን እንዴት፣ ወዴት፣ መቼ፣ ለምን፣ የት፣ ወዘተ. የሚሉትን የትርጉም ሁኔታ የሚወስን ነው፡፡ በግእዝ የተውሳከ ግስ ዐይነቶች ብዙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ዋና ዋናዎቹ የተውሳከ ግስ ዐይነቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### ፫.፱.፩.መካናዊ ተውሳከ ግስ

መካናዊ ተውሳከ ግሶች ቦታን የሚያመለክቱ የተውሳከ ግስ ዐይነቶች ናቸው፡፡

| መካናዊ ተውሳከ ግስ | ምሳሌ፡- |
|---|---|
| ህየ = እዚያ | ፩. በህየ ንበሩ፡፡ |
| ዝየ = እዚህ | ፪. አነ መጻእኩ ዝየ፡፡ |
| ላዕለ=ላይ | ፫. ገመቹ ነበረ ላዕለ ደብር |
| ለፌ ወለፌ=ወዲያና ወዲህ | ፬. ውእቱ ይመጽእ ከዋላ፡፡ |
| ከዋላ=በኋላ | ፭. አዳነች ነጸረት ለፌ ወለፌ |
| መንጸረ=በትይዩ | ፮. ቆመ መንጸረ ቤቱ፡፡ |
| ትርጋፀ=በግርጌ | ፯. ኖመ ትርጋፀ እገሪሁ ለአቡነ፡፡ |

### ፫.፱.፪.የጊዜ ተውሳከ ግስ

የጊዜ ተውሳከ ግሶች ጊዜን የሚያመለክቱ የተውሳከ ግስ ዐይነቶች ሲሆኑ፣ እንደ ስምና እንደ ተውሳከ ግስ በመሆን ያገለግላሉ፡፡

| የጊዜ ተውሳከ ግስ | | |
|---|---|---|
| ጌሠም=ነገ | ይእዜ=ዛሬ | ትካት= ጥንት፣ ቀድሞ |
| ዮም=ዛሬ | ኀሪፈ=ዘንድሮ | ዘልፈ=ዘወትር |
| ትማልም=ትላንት | ገሪፈ=አምና | ዘልፈ=ዘወትር |
| መዓልት=ቀን | መንፈቅ=ግማሽ ዓመት | ድኅረ=በኋላ |
| ሳኒታ=ማግስት፣ነገ | ድኅረ=በኋላ | ምሳሌ፡- |

| | |
|---|---|
| ፩. አቡየ ይመጽእ ጌሠመ፡፡ | ፮. ውእቱ ይመጽእ ሳኒታ ፡፡ |
| ፪. ዮም ተመይጠ ከበደ ኀበ ቤቱ፡፡ | ፯. አነ እመጽእ በጽባሕ ኀቤከ፡፡ |
| ፫. ዓለሙ መጽአ ትማልም፡፡ | ፰.ይእቲ ትመጽእ ድኅረ ጌሠም፡፡ |
| ፬. ሖረ መዓልተ ወሌሊተ፡፡ | ፱. ወተፈጸመ ቀዳማይ መንፈቀ ዓመት፡፡ |
| ፭. ትካት ዘንመ ማየ አይሀ፡፡ | ፲. አንተ ትገይስ ዘልፈ ኀበ ቤተ ትምህርት፡፡ |

## ፫.፲.መስተዋድድ

በስም ላይ እየወደቀ ዐረፍተ ነገርን የሚያሳካ ወይም የሚያዋድድ ቃል መስተዋድድ ተብሎ ይጠራል፡፡ በግእዝ ደቂቅ አገባብ ይባላል (ደቃቃ ማሳኪያ ማለት ነው)፡፡ የአንቀጽ ማሰሪያነትን አያስቀርም፡፡ በሚገባበት ዐረፍተ ነገር ሁሉ ከስም ቀድሞ ይገባል፡፡ ዋና ዋናዎቹ የመስተዋድድ ዐይነትና ክፍሎች በየቦታቸው ቀርበዋል፡፡

### ፫.፲.፩.የቦታ መስተዋድድ

የቦታ መስተዋድድ የሚባሉት የድርጊቱን ቦታ የሚያመላክቱ የመስተዋድድ ዐይነቶች ናቸው፡፡ መካናዊ መስተዋድድ ተብለው ይጠራሉ፡፡

| የቦታ መስተዋድድ | ምሳሌ |
|---|---|
| ውስተ=ውስጥ | ፩. ዓሣ ይነብር ውስተ ባሕር፡፡ |
| ዲበ=ላይ | ፪. መልአ ዐመፃ በዲበ ምድር፡፡ |
| ኀበ=ወደ | ፫. ዐለሙ ሖረ ኀበ አክሱም፡፡ |
| ማእከለ=መሐል | ፬. በማእከለ ክልኤ እንሰሳ ርኢኩከ ፡፡ |
| ላዕለ=ላይ | ፭. ዐርጉ መልዕልተ ደብር፡፡ |
| መልዕልተ=ላይ | ፮. አንስርት የዐውዱ ላዕለ ሰማይ፡፡ |
| ታሕተ=ከታች | ፯. ወንሰግድ ታሕተ መከየደ እገሪከ፡፡ |

### ፫.፲.፪.የጊዜ መስተዋድድ

የጊዜ መስተዋድድ የሚባሉት ድርጊቱ መቼ እንደ ተፈጸመ የሚገልጹ ወይም ጊዜን የሚጠቁሙ የመስተዋድድ ዐይነቶች ናቸው፡፡

| የጊዜ መስተዋድድ | ምሳሌ |
|---|---|
| ጊዜ=በቁሙ | ፩. ጊዜ ስድስቱ ሰአት መጽአ ቢጽየ እምነቤቱ፡፡ |
| ቀዲሙ=ፊት | ፪. አሜሃ ይበክዩ እኩያን፡፡ |
| ዘመን= ወቅት | ፫. ማእዜ ውእቱ ዕለተ ልደቱ፡፡ |
| አሜሃ= ያንጊዜ | ፬. ተሐውር ኵለሄ ኀበ ፈነውኩከ፡፡ |
| ትማልም=ትላንት | ፭. ቀደስነ ትማልም ከበደሃ፡፡ |
| ቅድመ = በፊት | ፮. አቅዲሙ ነገረ በጽባሕ፡፡ |
| ድኅረ= በኋላ | ፯. ድኅረ ነግሠ ቴዎድሮስ ነግሠ ዮሐንስ፡፡ |


AbeselomNekatibeb(nabeselom@gmail.com)

## ምልማድ

**ተርጉም ለእሉ ዐረፍተ ነገር ኀበ ልሳነ አምሐራ፡፡**

፩. ተለዓለ ሞገሰ ስሙ ተውላጠ ጻማሁ፡፡
፪. አስቴር ጻመወት ብዙኃ በእንተ ክብረ ኢትዮጵያ፡፡
፫. አነ እመጽእ በጽባሕ ኀቤከ ምስለ ቢጽየ፡፡
፬. ሽምሱ ዘተመይጠ እምነ ዐድዋ ወሐረ መንገለ አዲስ አበባ፡፡
፭. ውእቱ አንሶሰወ ኀበ ፈለገ ዓባይ ፡፡
፮. ይዘንም ዝናም ላዕለ ምድር፡፡
፯. ውእቶሙ ይነብሩ ውስተ ጽልመት፡፡
፰. ሕንጻ ፋሲለደስ ይትረከብ ማእከለ ትእይንታ ለጎንደር፡፡
፱. ሐነጸ ቤቶ ዲበ ኰክሕ፡፡

## ፫.፲፩.መስተፃምር

መስተፃምር ማለት የሚያያይዝ /የሚያጣምር ማለት ሲሆን ፣ ቃላትና ሐረግን ወይም ዐረፍተ ነገርን ለማያያዝ የሚያገለግል ቃል ነው፡፡ በአንቀጽ ላይ እየወደቀ ማሰሪያ አንቀጽ እንደያስር ያደርጋል፡፡ በግእዝ ዐቢይ አገባብ ይባላል፡፡

| መስተፃምር (ዐቢይ አገባብ) | | መስተፃምር (ንዑስ አገባብ) |
|---|---|---|
| አምጣነ=ና፣ ስለ፣ያህል<br>እስመ=ና ፣ እኮ<br>አኮኑ=ና<br>ዘ=የ<br>እንተ=የ<br>እለ=የ | ሶበ=ጊዜ<br>እመ=ጊዜ<br>በእንተ=ስለ<br>በይነ=ስለ<br>አመ= ጊዜ<br>መጠነ= ያህል፣ስለ<br>ህየንተ=ስለ | ዓዲ=ገና፣ ዳግመኛ<br>ባሕቱ=እንጂ፣ ነገር ግን<br>አላ= እንጂ፣ ነገር ግን<br>ዳእሙ=እንጂ<br>ወ=ና፣ ም<br>አው=ወይም<br>ዮጊ= ምናልባት |
| ዐቢይ አገባብ | | (ንዑስ አገባብ) |
| **ምሳሌ፡-**<br>፩. አንቀሐኒ ሊተ ሶበ ተሐውር ኀበ ቤተ ትምህርት፤<br>፪. ጊዜ መጻእከ አንተ ነበርኩ ውስተ ቤትየ፡፡<br>፫. እንግርከ አመ ይመጽእ ቢጽየ፡፡<br>እስመ መጽአ | | **ምሳሌ፡-**<br>፩. መጽኡ ሐጎስ ወሰሎሜ፡፡<br>፪. ዓዲ ናቄርብ ለከ ዘንተ፡፡ |

## ፫.፲፪.ቃለ አጋኖ

ነገርን ለማጋነን፣ ለማድነቅ፣ ለጸጸት ወዘተ. የምንጠቀምባቸው ቃላት ወይም ድምፅን አጎላምሰው የሚያናግሩ ሆሄያት ቃለ አጋኖ (አንክሮ) ይባላሉ፡፡ ከቃላት ክፍሎች አይመደቡም፡፡ ከታች ለአብነት የቀረቡትን ቃለ አጋኖዎችና ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

| ቃለ አጋኖ | ዐረፍተ ነገር | የመልእክቱ ዐይነት |
|---|---|---|
| ኬ= ዋ፣ ማ | ኬ→ውእቱኬ ዘሖረ፡፡ | አጋኖ፣ አንክሮ |
| ኣ=ቃለ መልእክት | ኣ→ሀበኒኣ፡፡ | ቃለ መልእክት |
| ኦ=ሆይ | መ→እፎመ ጸገብከ፡፡ | ዘለፋ |
| እፎ=እንዴት | ኑ→አይቴኑ ሀገርከ፡፡ | ጥያቄ |
| እንቋዕ=እንኳን፣ እሰይ | መ→እስኩመ ንግረኒ፡፡ | ጥያቄ |
| አሌ= ወዮ | እፎ→እፎ እፎ ፡፡ | ጥያቄ |
| እግዚኦ= አቤቱ | ሶ→ተመየጥሶ፡፡ | አክብሮ |
| ሶ=እባክህ ፣ ሳ | ኦ→ኦ አብዳን ኢትሌብውኑ፡፡ | ዘለፋ |

## ምልማድ ሣልሳይ

1. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገር ወደ ልሳነ ግእዝ ተርጉም

| | |
|---|---|
| ፩. ቀይ ባሕርን እንዴት ተሻገርከው፡፡ | ፭. ዕንኳን በሰላም ወደ ሀገርህ መጣህ፡፡ |
| ፪. ልጄ እባክህ ወደ ቤትህ ተመለስ፡፡ | ፮. አቤቱ ይቅር በለኝ፡፡ |
| ፫. ወደቀደመ ነገራችን እንመለስ፡፡ | ፯. ወንድሜ ሆይ ራትህን ብላ፡፡ |
| ፬. ወደኔ በፍጥነት ና ንጉሥ አለ፡፡ | ፰. ወዮልን ወዮታ አለብን፡፡ |

2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መብራሪያ ስጥ

፩. አፍአዊ ውላጤና ውሳጣዊ ውላጤ ምን ማለት እንደሆነ አብራራ፡፡

፪. ስም በሳድስ ሲደርስ እንዴት ይበዛል? በምሳሌ አሳይ፡፡

፫.የሚከተሉትን ቃላት በነጠላ ጻፍ፡፡ አክናፍ፣ ከለባት አምሳል አስናን ዐቢያን፡፡

፬. የግስ ዐይነቶች ስንት ናቸው? ስማቸውን ጥቀስ፡፡

፭. በአስሩ መራሕያን የሚከተሉትን ግሶች (ነጸረ፣ ወለደ፣ ከፈለ፣ መሐረ) አርባ፡፡

፮. የርባ ቅምርና የርባ ግስ ልዩነት ምንድነው ? አብራራ፡፡

፯. የበጽሐ፣ የደንገፀ፣ የሰበረን ቦዝ አንቀጽ በአዕማድ አርባ፤

፰. ቅጽል ከምን ከምን ይገኛል ግለጽ።

፱. የስም ክፍሎች ስንት ናቸው ስማቸውን በመጠቀስ አበራራ፡፡

# ምዕራፍ አራት

**<u>፬.ዐረፍተ ነገር</u>**

ዐረፍተ ነገር በሥርዓት ተቀነባብሮ ሙሉ ሰሜት ሊሰጥ የሚችል የቃላት ወይም የሐረጎች ስብሰብ ነው፡፡

**<u>፬.፩.የዐረፍተ ነገር መዋቅር</u>**

በግእዝ ቋንቋ ዐረፍተ ነገር አመሠራረት ማሰሪያ አንቀጽ ሲቀድም ባለቤትና ተሳቢ (ግስ+ ባለቤት+ ተሳቢ) ይከተላሉ ፡፡ ባለቤት ሲቀድም ደግሞ ማሰሪያ አንቀጽና ተሳቢ (ባለቤት+ ግስ +ተሳቢ) ይከተላሉ፡፡ በተጨማሪም ተሳቢ፣ ማሰሪያ አንቀጽ፣ ባለቤት(ተሳቢ +ግስ+ ባለቤት) ሆኖ ሊመሠረት ይችላል፡፡ ለዚህም የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት፡፡

**<u>፩. ባለቤት/በዐለቤት፡-</u>** ግስ ከነጓዙ የሚነገርለት ቃል ባለቤት ይባላል፡፡

| ባለቤት ሲቀድም | ማሰሪያ አንቀጽ | ተሳቢ |
|---|---|---|
| አበበ | መልሐ | ሰይፈ |
| ሙሴ | ከፈለ | ባሕረ |
| ሐጎስ | ረከበ | ዕንቄ |

፪. **<u>ማሰሪያ አንቀጽ</u>**

| ማ.አንቀጽ ሲቀድም | ባለቤት | ተሳቢ |
|---|---|---|
| ከፈለ | ሙሴ | ባሕረ |
| መልሐ | አበበ | ሰይፈ |
| ረከበ | ሐጎስ | ዕንቄ |

**፫.ተሳቢ፡-** ገቢር (ርቱዕ ተሳቢ)ና ተገብሮ (ኢርቱዕ ተሳቢ) ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ ተሳቢ በዐረፍተ ነገር ውስጥ የገቢርና ተገብሮ ሕግ መጠበቅ አለበት፡፡ ገቢር ለማናገር ሲፈለግ ሕግጋቱን ጠብቀው በሰንጠረዡ ውስጥ እንደ ተመለከተው ይለወጣል፡፡

| ተለዋጭ ፊደላት | ተገብሮ | ገቢር |
|---|---|---|
| ካዕብ> ሳብዕ | ግብሩ | ግብሮ |
| ግልስ> ኃምስ | ከይሲ | ከይሴ |
| ሳድስ> ግእዝ | ኅብስት | ኅብስተ |
| ኃምስ= ኃምስ | ጽጌ | ጽጌ |
| ራብዕ= ራብዕ | እንዚራ | እንዚራ |
| ሳብዕ= ሳብዕ | ከበሮ | ከበሮ |

| ተሳቢ ሲቀድም | ማሰሪያ አንቀጽ | ባለቤት |
|---|---|---|
| ሰይፈ<br>ኀብስተ<br>ጦማረ | መልሐ<br>በልዐ<br>ጸሐፈ | አበበ<br>ዘውዱ<br>ግርማ |

ገቢር በተጸውዖ ስም ላይ "ሀ" ይጨምራል፡፡ ምሳሌ፡- ሞገስ አፍቀረ አስቴርሀ፡፡

ተገብሮ(ኢ.ርቱዕ ተሳቢ) ለምሳሌ፡- ተሐንጸ ቤት፡፡

፩.ዘርፍ፡-ባለገንዘብነትን ይዞ ከባለቤቱ ወይም ከተሳቢው ቀጥሎ የሚመጣ ስም ዘርፍ ይባላል፡፡ ባጠቃላይ ዘርፍ በአገባብ ተያይዞ በአራት ፊደላት ተናቦ የሚነገር የሰዋስው ሥርዓት ነው፡፡ ለምሳሌ የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

| ባለቤት | ማሰሪያ አንቀጽ | ተሳቢ | ዘርፍ |
|---|---|---|---|
| ጋዲሳ | ሐነጸ | ቤተ | ተውኔት |
| አብደላ | ቀተለ | አርዌ | ምድር |
| ሐጎስ | አጥረየ | ከበሮ | ማኅሌት |

## ፬.፪. ኀብራተ ዐረፍተ ነገር (የዐረፍተ ነገር ዐይነቶች)

ዐረፍተ ነገር ሁሉ አንድ ዐይነት ተግባር የለውም፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ዐረፍተ ነገር እንደየተግባሩና ዐይነቱ በተለያየ ክፍል ይመደባል፡፡ ዋና ዋናቹ የዐረፍተ ነገር ዐይነቶች መተርክ (ሐተታዊ)፣ መጠይቅ (ጥያቄያዊ) እና መአዘዝ (ትእዛዛዊ) ተብለው በሦስት የሚከፈሉ ሲሆን፣ በአሉታና በአዎንታ ይነገራሉ፡፡

### ፬.፪.፩.መተርክ ዐረፍተ ነገር

መተርክ ዐረፍተ ነገር ወጋዊ፣ ተረታዊ፣ ሐተታዊ ማለት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ንግግር የሚደረገው በዚህ ክፍል ነው፡፡ መተርክ ዐረፍተ ነገር በአዎንታና በአሉታ ሊቀርብ ይችላል፡፡

#### ፩. አዎንታ መተርክ

አዎንታ ማለት እውነት፣ አዎን ማለት ነው፡፡ የአሉታ ተቃራኒ ነው፡፡ አወንታዊ ዐረፍተ ነገር አንድ ድርጊት በተወሰነ ቦታና ጊዜ በተለያየ ምክንያት መፈጸሙን የሚገልጽ ነው፡፡

| | |
|---|---|
| • ሳሙኤል ኀረየ ሰብአ፡፡<br>• ቦ ሰብአ በዝንቱ ብሔር፡፡<br>• ወረደ ብእሲ ኀበ ፈለግ፡፡ | ፀማዕኩ ወአስተይክሙኒ፡፡<br>አስቴር ወሰሎሜ ፈጸማ ግብሮን፡፡ |

## ፪. አሉታ መተርክ

አሉታ ሚለው ቃል አሌ ከሚለው ቃል የተገኘ ነው፡፡ አሌ ማለት አይደለም፣ አልሆነም ማለት ሲሆን፣ አሉታ ማለት አፍራሽ ማለት ነው፡፡ አሉታ ዐረፍተ ነገር በአዎንታ ዐረፍተ ነገር የቀረበ ሐሳብን የሚያፈርስ የአዎንታ ተቃራኒ ነው።

ምሳሌ፡- አኮ መርድእ ውእቱ፡፡
አልቦ አንስት ውስተ ጉባኤ፡፡
አበበ ኢይጽሕፍ ጦማረ፡፡
ኢተመይጠ አቡየ እምሐዊሮቱ፡፡
አኮ አነ ዘገበርኩ ዘንተ ግብረ፡፡

### ፩.፪.፪.መጠይቅ ዐረፍተ ነገር

| ፩. መጠይቅ አዎንታ | ፪. መጠይቅ አሉታ |
|---|---|
| አይቴኑ ተሐውር ቢጽየ፡፡ | ኢሖረኑ አቡከ ኀበ አዋሳ፡፡ |
| ማእዜ ተመየጥከ እምነ ጎንደር፡፡ | ኢትመየጥኪኑ ኀበ ግብርኪ፡፡ |
| አንተሁ ትንእስ እምአብያጺከ፡፡ | አኮሁ አዋልዲሁ ለከበደ፡፡ |
| ለምንት ይዜኃር ኃያል በኀይሉ፡፡ | አልቦሁ ዘመድ በዝንቱ ብሔር፡፡ |
| መኑ ውእቱ ዝንቱ ዘነበረ ምስሌከ፡፡ | ኢትትናገርኑ ዐረበ ወአምሐራ፡፡ |
| እፎ ኀደጉ አርድእት ሀገሮሙ፡፡ | አልቦሁ ግብር ለዝኩ ብእሲ፡፡ |
| እለ መኑ እሙንቱ አብያጽየ፡፡ | |

### ፩.፪.፫.መአዘዝ ዐረፍተ ነገር

| ፩. መአዝዝ አዎንታ | ፪. መአዝዝ አሉታ |
|---|---|
| ጸሐፍ ጦማረ ለአቡከ፡፡ | ኢትሑር ኀበ ሀገረ ባዕድ፡፡ |
| ንበር ዝየ ወግበር ዘንተ፡፡ | ኢትስተይ ወይነ፡፡ |
| ፈክር ለነ ዘንተ መጽሐፈ፡፡ | ኢትደይ እዴከ ላዕለ ወልድከ፡፡ |
| ሑር ኀበ አንኮበር ከመ ትትመሀር ሰዋስወ ግእዝ፡፡ | ኢትቅትል ሰብአ፡፡ |


AbeselomNekatibeb(nabeselom@gmail.com)

## ፬.፫.ክፍለ ዐረፍተ ነገር

የዐረፍተ ነገር ክፍል ንኡስ ፣ ምክዕቢት እና ዐቢይ ዐረፍተ ነገር ተብሎ በሦስት ይከፈላል፡፡

### ፬.፫.፩. ንኡስ ዐረፍተ ነገር

ንኡስ ዐረፍተ ነገር ባለቤትና ግስ የያዘ ነው፡፡ለምሳሌ፡-
፩. መጽአ መምህር ፫. ዘበጠ ከበሮ ፪. ቀተልኩ ከይሴ

### ፬.፫.፪. ምክዕቢት ዐረፍተ ነገር

ምክዕቢት ማለት እጥፍ፣ ድርብ ማለት ነው፡፡ይህ ክፍለ ዐረፍተ ነገር በንኡስ አገባብ ይያያዛል፡፡ ድርብ ዐረፍተ ነገር እንደ ማለት ነው፡፡

ምሳሌ፡- ፩. ወልድ ሰአለ አሐደ ጥያቄ ወአቡሁ አውሥአ ሎቱ

፪. አነ ሖርኩ ኀበ ናዝሬት ባሕቱ ኢረከብኩ እኁየ፡፡

፫. ዓለሙ መጽአ ኀበ ቤቱ ባሕቱ መልካሙ ሖረ ኀበ ቤተ ሶከር፡፡

### ፬.፫.፫. ዐቢይ ዐረፍተ ነገር

ዐቢይ ዐረፍተ ነገር ማሰሪያነቱን ዐቢይ አገባብ ወድቆ ያስቀረበትን ዐቢይ ሐረግ በውስጡ የያዘ ክፍለ ዐረፍተ ነገር ነው፡፡

ምሳሌ፡- ፩. ሶበ ይመጽእ አቡየ እነግሮ፡፡

፪. አእምሮ ለዘሖረ ትማልም እኁከ፡፡

፫. ነሐውር ንሕነ ሶበ ይመጽአ እማንቱ፡፡

፬. ነጸርኩ እዴሁ ለዘተሰብረ በሠረገላ ምድር፡፡

## ፬.፬. ሐረግ

ሐረግ ከቃላት የሚመሰረትና ከቃል ሰፋ ያለ ከዐረፍተ ነገር ያነሰ የመዋቅር ዐይነት ነው፡፡ የሚመሠረተውም የቃላትን ክፍሎች መሠረት አድርጎ ነው፡፡ ሐረግ ንኡስ ሐረግ፣ ዐቢይ ሐረግ፣ ስማዊ ሐረግ፣ ወዘተ. ተብሎ ሊከፈል ይችላል፡፡

### ፩. ንኡስ ሐረግ

ንኡስ ሐረግ ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ የሌለው የቃላት ክምችት/ስብስብ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ፩. ዲበ ምድር ፫. ማእከለ ባሕር
፪. ላዕለ ሰግላ ፬. ሐዊረ ፍኖት

### ፪. ዐቢይ ሐረግ

ዐቢይ ሐረግ ባለቤትና አገባብ የወደቀበት አንቀጽ ከነተሳቢው የያዘ የሐረግ ክፍል ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ፩. ዘዐርገ ላዕለ ሰግላ፪. ዘይነብር ዲበ ምድር ፡፡ ፫. እንተ ቆመት ማእከለ ፍኖት፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ፩. ተግባራዊ ሰዋስው

### ፩.፩. የሰላምታ ዐይነቶች

የሰላምታ ዐይነቶች አራት ናቸው፡፡ እነርሱም፦

ሰላም ለከ -------እንዴት አደርህ/ ዋልህ/ አመሻችሁ/ ዋሉ

ሰላም ለኪ--------እንዴት አደርሽ/ ዋልሽ/ አመሻችሁ/ ዋሉ

ሰላም ለክሙ------እንዴት አደራችሁ/ ዋላችሁ/ አመሻችሁ/ አረፈዳችሁ (ተ.ብ)

ሰላም ለክን--------እንዴት አደራችሁ/ ዋላችሁ/ አመሻችሁ/ አረፈዳችሁ (አ.ብ)

በተጨማሪም  በግእዝ የሰላምታ አይነት "በሐ" ነው፡፡ በአራት ቅርቦች ይዘረዝራል፡፡

በሐከ---------እንዴት አደርህ/ ዋልህ/ አመሻችሁ/ ዋሉ

በሐኪ--------እንዴት አደርሽ/ ዋልሽ/ አመሻችሁ/ ዋሉ

በሐክሙ------እንዴት አደራችሁ/ ዋላችሁ/ አመሻችሁ/ አረፈዳችሁ/ ጤና ይስጠልኝ (ተ.ብ)

በሐክን-------እንዴት አደራችሁ/ ዋላችሁ/ አመሻችሁ/ አረፈዳችሁ/ ጤና ይስጠልኝ (አ.ብ)

## ሀ. ንግግር (ጭውውት)

**ኪሮስ**

- ሰላም ለከ ዓለምነህ
(ሰላም ላንተ ይሁን ዓለምነህ)
- እሉ አብያጺከ ውእቶሙ
(እነዚህ ጓደኞችህ ናቸው)
- አይቴ ብሔሮሙ
(የት ነው ሀገራቸው)
- ይትሜሀርኑ ትምህርተ ዘመነዌ
(የዘመናዊ ትምህርት ይማራሉ)
- አይቴ ውእቱ ቤተ ትምህርቶሙ
(ትምህርት ቤታቸው የት ነው)
- እፎ ውእቱ ትምህርት
(ትምህርት እንዴት ነው)
- ናሁ አይቴ ተሐውር
(አሁን ወዴት ነው የምትሔደው)
- በል ሠናይ ፍኖት
(በል መልካም መንገድ)

**ዓለምነህ**

- ወሰላም ለከ ኪሮስ
(ሰላም ላንተም ኪሮስ)
- እወ
(አዎ)
- ዝ እምወሊ ጋ ወዝኩሰ እምጎንደር
(ይህ ከወሊጋ ነው ያ ደግሞ ከጎንደር)
- እወ ይትሜሀሩ እሙንቱ ትምህርተ ዘመነዌ
(አዎ የዘመናዊ ትምህርት ይማራሉ)
- አክሱም ቤተ ጉባኤ ውእቱ ቤተ ትምህርቶሙ
(ት/ ቤታቸው አክሱም ዩኒቨርሲቲ ነው)
- ሠናይ ወእቱ
(ጥሩ ነው)
- አነ አሐውር ምስሌሆሙ ኀበ ቤተ ትምህርትየ
(ከነሱ ጋር ወደ ት/ ቤቴ እየሔድኩ ነው)
- አሜን
(ይሁን ይደረግልኝ)

## ለ. ሰላምታ

**ሳሙኤል** **አበበች**

ሰላም ለኪ አበበች ---------------------------------------ወሰላም ለከ ሳሙኤል፡፡
ለምንት መጻእኪ መካነ አእምሮ ዘጎንደር፡፡-አንሰ መጻእኩ ለተምህሮ ልሳነ አምሐራ
ማእዜ ውእቱ ዘወጠንኪ ለተምህሮ---------------ዘዮም ዐመት ወጠንኩ፡፡
አንቲ ውእቱ ትጉህ ------------------------------ እወ ጥበብ ይኄይስ እምኩሉ፡፡
ትምህርትሰ እፎ ውእቱ------------------------------ሠናይ ውእቱ ሳሙኤል፤
አንሰ ኀሠሥኩኪ ትማልም ዳዕሙ ኢነበርኪ-------እወ ኢነበርኩ እምነ ማኅደርየ፡፡
አይቴ ነበርኪ-----------------------------------------ቦ አነ ውስተ ቤተ መጻሕፍት፤
ምስለ መኑ---------------------------------------------ምስለ ቢጽየ ዘትትበሀል በለጡ፤
ናሁ አይቴ ዘተሐውሪ-------------------------------------ኀበ ቤተ ተውኔት
አሐውር ምስሌኪ------------------------------------------ኦሆ፤
ድኅረ ቤተ ተውኔት አይቴ ውእቱ ዘተሐውሪ-------ኀበ ቤተ መጻሕፍት፤
በህየ ምንተ መጽሐፈ ውእቱ ዘታነብቢ---------------ሰዋስወ ግእዝ፤
በሊ ድኅረ ምሳህ ንትራከብ--------------------------------አአቅበከ፤
ለእመ ኢንትራከብ ሠናይ ንባብ------------------------ለክልኤነ፤

## ሐ. ትውውቅ

ሰላምተኛ (አልማዝ)፦ጥዒና የሀብ ልየ------------------ለኩልነ፤
መልስ ሰጭ (ከበደ)፦ወሰላም ለኪ እኅትየ = (ሰላም ላንቺም እኅቴ)
ሰላምተኛ፦ መኑ ወእቱ ስምከ እኁየ= (ስምህ ማን ነው ወንድሜ)
ከበደ፦ ከበደ ውእቱ ስምየ = (ስሜ ከበደ ነው)
አልማዝ፦ ስምየ ውእቱ አልማዝ፤ እምአይቴ መጻእከ=
ስሜ አልማዝ ነው፤ ከየት ነው መጣኸው)
ከበደ፦ እምናዝሬት= (ከናዝሬት)
አልማዝ፦ ናሁ አይቴ ተሐውር= (አሁን የት ነው የምትሄደው)
ከበደ፦ ኀበ መቀሌ =(ወደ መቀሌ)
አልማዝ፦ ለምንት ተሐውር ኀበ መቀሌ= (ወደመቀሌ ለምንድነው የምትሄደው)
ከበደ፦ ለጠይቆተ አዝማድየ= (ዘመዶቼን ለመጠየቅ)
አልማዝ፦ እስፍንቱ አዝማኒከ= (እድሜህ ስንት ነው)
ከበደ፦ ዕሥራ ወኀምስቱ =(ሃያ አምስት)
አልማዝ፦ መርድአ ኮሌጅ አንተኑ= (የኮሌጅ ተማሪ ነህ)
ከበደ፦ እወ አነ= ( አዎ ነኝ)
አልማዝ፦ አይቴ ውእቱ ቤተ ትምህርት= (ትምህርት ቤትህ የት ነው)
ከበደ፦ ደብረ ብርሃን መካነ አእምሮ ውእቱ ቤተ ትምህርትየ= (ትምህርት
ቤቴ ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡)

አልማዝ፦ እስፍንተ ዓመተ በጻሕከ= (ስንተኛ ዓመት ደረስክ)
ከበደ፦ ሥልሰ ዓመተ በጻሕኩ =(፫ ዓመት ሆኖኛል)
አልማዝ፦ ተአምርኑ ልሳነ ግእዝ= (የግእዝ ቋንቋ ታውቃለህ ?)
ከበደ፦ እወ ንስቲት ንስቲት አአምር =(አዎ ጥቂት ጥቂት አውቃለሁ )
አልማዝ፦ በል ኩን ትጉህ =(በል ትጉህ ሁን)
ከበደ፦ ኦሆ እኅትየ= (እሺ እኅቴ)

## ፭.፪. ጦማር

**ጦማረ አብዲሳ እምአሰላ**

**ሀ. ለሀብቶም ዘአክሱም**

ሰላም ለከ ሀብቶም እኁየ፡፡ እፎኑ ሀለውከ ፡፡ አነ ጸሐፍኩ ለከ ዘንተ ጦማረ ለካልኣይ ጊዜ ፡፡ ለምንትኑ አንተ ዘኢትጽሕፍ ሊተ፡፡

ትምህርት እፎ ውእቱ፡፡ ማእዜ ወእቱ ፈተናከ፡፡ ንሕነ ፈጸምነ ፈተናነ ናሁ ዕረፍት ውእቱ፡፡ ሀብቶም! ማእዜ ውእቱ ተባርኮ አነ እመጽእ ኀቤከ ምስለ ቢጽየ አበበ፡፡ እስኩ ጸሐፍ ሊተ፡፡ ፈኑ ሊተ መጻሕፍተ ሰዋስወ ግእዝ ወቅኔያተ፤ ወአነ እፌኑ ለከ ዘሀለዉ ምስሌየ፡፡ ሀብቶም እስከ ንትራከብ በሰላም ሠናይ ጊዜ ይኩን ለከ፡፡

አብዲሳ እምአሰላ

**ምልማድ**

ደብዳቤውን መሠረት በማድረግ ለጓደኛህ ደብዳቤ ጻፍ፡፡-------------------------፡፡


AbeselomNekatibeb(nabeselom@gmail.com)

ምንባብ ሁለት

አነ መርድእ ዘራብዕ ክፍል አትነሣእ በጽባሕ ወእትሀጸብ ገጽየ፡፡ እስመ ርሁቅ ውእቱ ቤተ ተምህርትየ፡፡ ወእለብስ ልብስየ ወእምድኅረ ለበስኩ ልብስየ አሐውር እሂዝየ መዝገበ ዘመጻሕፍትየ፡፡ ወእንዘ አሐውር እረክብ አብያጽየ በውስተ ፍኖት፡፡ ወነሐውር ኅቡረ እንዘ ንትዋነይ በእንተ ትምህርት፡፡ ወአመ ንበጽሕ ቤተ ትምህርት ንበውእ ቅጽረ፡፡

ወእንዘ ንሰምዕ ድምፀ መጥቅዕ ንበውእ ፍጡነ በበክፍልነ። ወእምድኅረ ቦኡ ይበውእ መምህር ኀበ ክፍል። ወንትነሣእ ሎቱ ኅቡረ እስመ ክቡር ውእቱ መምህር። ወይብል "ሰላም ለክሙ አርድእት" ወንሕነኒ ንበል "ሰላም ለከ መምህር" ወካዕበ ይብለነ "ንበሩ" ወንነብር ንሕነ በበመካንነ፡፡

ወዘእንበለ ይጠን ሐዲሰ ትምህርተ ውእቱ ይሴአለነ እንዘ ይብል "መኑ ይነግረኒ ዘመሀርኩክሙ ትማልም"፡፡ ወካዕበ ይሴአለነ አሐደ ጥያቄ ኀሊፎ ኀሊፎ። ወኀዳጣን እምኔነ ያውሥኡ ሎቱ፡፡ ወእምዝ ይሜህረነ ሐዲሰ ትምህርተ ወናጸምዕ እንዘ ይሜህረነ ውእቱ መምህር ወንጽሕፍ ዘይጽሕፍ ለነ፡፡

(ከግእዝ መግቢያ መጽሐፍ የተወሰደ)

ምልማድ

፩. ከምንባቡ ውስጥ የሚገኙትን መጠይቃዊና ትእዛዛዊ ዐረፍተ ነገር ለይተህ አሳይ፡፡

፪.በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ዐቢይ አገባብ፣ ንኡስ አገባብና መስተዋድዳን ቃላትን አውጥተህ ጻፍ፡፡------------------------------------------------------------------------------፡፡

## ምንባብ አራት፡- ግጥም

| | |
|---|---|
| ምድር ትቤ ይኩነኒ ገላውዴዎስ፣<br>ዘይትለሀይ በፀዓዳ ፈረስ፡፡<br>ዘተወልደ በጅርምይ ሜዳ፣<br>ገላውዴዎስ ወልድ ማኼዳ፣<br>ድል ይነዳ በፈረስ ፀዓዳ፡፡<br>(ከገላውዴዎስ ዜና መዋእል የተወሰደ) | ሰዐምኒ እሑር በስቍረተ ዕፅ ዓነደ፣<br>አቡኪ ወእመ ዚአኪ ኢሠምሩ እንግዳ፡፡<br>ትርጉም<br>እናትና አባትሽ አይወዱም እንግዳ፣<br>ሳሚኝና ልሂድ በሳንቃው ቀዳዳ፡፡ |

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን ማብራሪያ በመስጠት መልስ፡፡

፩. በግእዝ የሚነገሩ የሰላምታ ዐይነቶች ስንት ናቸው? ዘርዝር፡፡

፪. ከግጥሙ ምን ተረዳህ? አብራራ፡፡

## ቃላት ወግስ ማጥኛ

| ቁ. | ግእዝ | ትርጉም | ግእዝ | ትርጉም | ግእዝ | ትርጉም | አኃዝ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሀከየ | ሰነፈ | ኀቡእ | ድብቅ | ድኀር | ጀርባ | ፩ |
| 2 | ሀየየ | ናቀ | ርዙም | ረጅም | ጥብ | ጡት፣ | ፪ |
| 3 | ህላዌ | መኖር፣ኑሮ | ርሒብ | ሰፊ | ኅጽው | ስልብ | ፫ |
| 4 | ለሰነ | ተናገረ | ገዚፍ | ወፍራም | ከብድ | ጉበት | ፬ |
| 5 | ላህየ | አጫወተ | ክቡድ | ከባድ | ወለጠ | ለወጠ | ፭ |
| 6 | ሐረበ | ወጋ፣ተዋጋ | ኀየፀ | ነደፈ፣ወጋ | ወረቀ | ተፋ | ፮ |
| 7 | ሐፀነ | አሳደገ | ኀይመት | ድንኳን | ነከሰ፣ ነሰከ | ነከሰ | ፯ |
| 8 | መልአ | መላ | ጸቢብ | ጠባብ | ጠበወ፣መጸ | ጠባ | ፰ |
| 9 | መሰለ | መሰለ | ቀጢን | ቀጭን | ወረቀ | ተፋ | ፱ |
| 10 | መንክር | ድንቅ | ነቅሐ | ነቃ፣ባነነ | ቀአ | አስታወከ | ፲ |
| 11 | ማእምር | አዋቂ | ነሰወ | ፈተነ | ነፍኀ | ነፋ | ፳ |
| 12 | ምጽዋት | ምጽዋት | ነቅዕ | ምንጭ | ተንፈሰ | ተነፈሰ | ፴ |
| 13 | ሞዓ | አሸነፈ | አስተናበረ | አዘጋጀ | ሰሐቀ | ሳቀ | ፵ |
| 14 | ሠገረ | ተራመደ | አሰረ | አሰረ | ወርአ | ሰወረ | ፶ |
| 15 | ሰገም | ገብስ | አሰም | ቅመም | ውሒዝ | ፈሳሽ | ፷ |
| 16 | ረመለ | አፈሰ፣ጫነ | አንፍ | አፍንጫ | ዐም | ነገድ | ፸ |
| 17 | ርደት | መውረድ | አፈው | መዓዛ | ፔርካ | ሽምብራ | ፹ |
| 18 | ቀብአ | ቀባ | እንክ | እንግዲህ | ጼነወ | አሸተተ | ፺ |
| 19 | ቀርሐ | ነጨ፣ላጨ | ኦኬ | ወይ! | ፈርሀ | ፈራ | ፻ |
| 20 | ቀነጸ | ዘለለ | ከለለ | ጋረደ | ደረጸ | ቀማ | ፼ |
| 21 | ቅድም | ፊት፣ጥንት | ከለበ | ቸኮለ | ደበወ | አደባ | ፲፼ |
| 22 | በለቀ | አደገ | ከለየ | ሰፈረ | ድድቅ | ድንገት | ፻፼ |
| 23 | በልየ | አረጀ | ከልዐ | አወለቀ | ዳዕሮ | ዋርካ | ፲፻፼ |
| 24 | በርዐ | ተንቀጠቀጠ | ከመመ | ቆረጠ | ተበአሰ | ተዋጋ | ፼፼ |
| 25 | ቤለ | አለ፣ተናገረ | ከሚን | ፌጦ | አድሐነ | አደነ | ፲፼፼ |
| 26 | ቤዛ | ካሳ | ክሣድ | አንገት | ደብደበ | መታ | ፻፼፼ |
| 27 | ቦሐ | ታየ፣ተገለጠ | ክቡድ | ከባድ | ቀረጸ | ቈረጠ | ፲፻፼፼ |
| 28 | ቦከ | ደዌ | ኮሬ | ጋን | ሠጸረ | ሠነጠቀ | ፼፼፼ |
| 29 | ተለወ | ተከተለ | ኩን | ሁን | ደጐጸ | ወጋ | ፲፼፼፼ |
| 30 | ተሐተ | ወረደ፣ | ወለ | ዋለለ | ሐንፈጠ | ጫረ | ፻፼፼፼ |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 31 | ተረበ | ተረበ፥ቀለደ | ወሃቢ | የሚሰጥ | ፈሐረ | ቆፈረ | ፲፻፼፼፼ |
| 32 | መጽለወ | ጠወለገ | ልሕጽ | የዛፍ ልጥ | ጸበተ፥ጸበየ | ዋኘ | ፼፼፼፼ |
| 33 | ሥረው | ስር | ጽጌ | አበባ | ሳረረ፥ጠየረ፥ | በረረ | ፲፼፼፼፼ |
| 34 | ረሰየ | አደረገ | ሣዕር | ሣር | ጸሊሓ | ጭቃ | ፻፼፼፼፼ |
| 35 | ተከለ | ተከለ | ሐብል | ገመድ | ጸምዐ | አዳመጠ | ፲፻፼፼፼፼ |
| 36 | ነበበ | ተናገረ | ገልድ | ቆዳ | ፀበነ | ያዘ | ፼፼፼፼፼ |
| 37 | ጸርሐ | ጠራ | ሥጋ | ሥጋ | ፀዋግ | ክፉ፥ጨካኝ | ፲፼፼፼፼፼ |
| 38 | ፀራዊ | ጠላት | ደም | ደም | ፈለየ | ለየ | ፻፼፼፼፼፼ |
| 39 | ገሀደ | ገለጠ | ዐፅም | አጥንት | ፈረየ | አፈራ | ፲፻፼፼፼፼፼ |
| 40 | ገሀፈ | በተነ | ሥብሕ | ስብ | ፎዝ | መወልወያ | ፼፼፼፼፼፼ |
| 41 | ገለወ | ሸፈነ | ጠነይ | ዋሻ፥ጎሬ | ፎደት | ኳስ | ፲፼፼፼፼፼፼ |
| 42 | ጐያ | ሸሸተ፥ስደት | ቀርን | ቀንድ | አኀዘ | ያዘ | ፻፼፼፼፼፼፼ |
| 43 | ጋእዝ | ጠብ፥ክርክር | ዘነብ | ጅራት | ሎሀ | ጻፈ | ፲፻፼፼፼፼፼፼ |
| 44 | ተከዚ | ወንዝ | ላባ | ላባ | ሐሰየ | ፈተገ | ፼፼፼፼፼፼፼ |
| 45 | ባሕር | ሐይቅ | ጸጕር፥ስዕር | ጸጉር | ኀፀበ | አጠበ | ፲፼፼፼፼፼፼፼ |
| 46 | ኀሜዕ | ሸምበቆ | ጠወቀ | አስጨነወ | መስእርት | ሚዶ | ፻፼፼፼፼፼፼፼ |
| 47 | ዔው | ጨው | ጥዕመ | ቀመሰ | ሰሐበ | ሳበ | ፲፻፼፼፼፼፼፼፼ |
| 48 | ወርሕ | ጨረቃ | ጠፍሐ | መታ | ገፍዐ፥ደፍዐ | ገፋ | |
| 49 | እንከ | እንግዲህ | ጣቃ | ጭለማ | ጠሐለ | ጣለ | |
| 50 | ኮክህ | አለት | ጥቃ | ቅርብ | መጠወ | ሰጠ | |
| 51 | ነቅዐ | መነጨ | ጠዋዒ | ንፉግ | ሰፈየ | ልብስ ሰፋ | |
| 52 | ኀል | በረት | ልሳን | ምላስ | ቀመረ | ቆጠረ | |
| 53 | ነፈቀ | ከፈለ | ጽፍር | ጥፍር | ጸንገለ | ተረጎመ | |
| 54 | ዘመነ | ዘመን ቆጠረ | ጸራሂ | መቅደስ | ሐለየ፣ ዘመረ | ዘፈነ | |
| 55 | ጠብዐ | ጨከነ | ቀይጽ | ባት | ላሀየ | ተጫወተ | |
| 56 | ገዘመ | ቆረጠ | ብርክ | ጉልበት | ጸለለ | ተንሳፈፈ | |
| 57 | ዘብሐ | አረደ | እድ | እጅ | ውኀዘ | ፈሰሰ | |
| 58 | ጸልአ | ጠላ | ክንፍ | ክንፍ | ቈረ | በረደ | |
| 59 | ፀመወ | አከመ | ጼርካ | ሽምብራ | ሐበጠ | አበጠ | |
| 60 | ፈተወ | ወደደ | አማዑት | ሆድቃ | ጸርቀመ | ጻፈ | |

## ዋቢ መጻህፍት

በላይ መኮንን (2001) ፤*ትንሣኤ ግዕዝ (አማርኛ-ግዕዝ መዝገበ ቃላት)*። አዲስ አበባ፡፡
-------------(2002)፤ *ሕያው ልሳን (ግዕዝ አማርኛ መዝገበ ቃላት)*፡፡ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡
አቤሴሎም ነቃጥበብ ።(2009)። *መሠረታዊ ሰዋስወ ግእዝ ።* አዲስ አበባ፤ፋር ኢስት ማተሚያ ቤት።
አለማየሁ ሞገስ (1950)፤*ሰዋስወ ግእዝ*፡፡አዲስ አበባ፤ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡
አምሳሉ አክሊሉ(1979)፤ *የኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ቅኝት፣ (ያልታተመ የማስተማሪያ ጥራዝ)፡፡* አድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።
አስረስ የኔሰው (1951)፤*የካም መታሰቢያ፡፡ አሥመራ* ፣ ኮከብ ጽባሕ ማተሚያ ቤት ዘማኀበረ ሐዋርያት፡፡
ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948)፤ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።
ናሁ ሠናይ ቀለመ ወርቅ (2008)፤*ሠረቀ ጸሐይ (መርሀ ሰዋስው ወግስ ወፍኖተ-ቅኔ)፡፡ አዲስ* አበባ፣አፍሪካ ማተሚያ ቤት፡፡
ዘርዓ ዳዊት አድሃና (1997)፤*መርኆ ሰዋስው ዘልሳነ ግእዝ፡፡* አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡
ዜና ማርቆስ እንዳለ (1989)፤*ጥንታዊ ግእዝ በዘመናዊ ዘዴ፡፡* አዲስ አበባ፤ አርክቲክ ማተሚያ ቤት፡፡
------------(2001) *የግእዝ ቋንቋ መግቢያ (ክፍል ሁለት)* ፡፡አዲስ አበባ ትንሣኤ ማተሚያ ቤት፡፡
ያሬድ ፋንታ (1989) ፤*ፍኖተ ግእዝ።* አስመራ፤ ፍራንስችስካና ማተሚያ ድርጅት።
ይትባረክ መርሻ (1995)፤ *የግእዝ አገባብና የቅኔ መንገዶች፡፡* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡
ደሴ ቀለብ (2002)፤ *ትንሣኤ ግእዝ*፡፡ አዲስ አበባ፤ አማኑኤል ማተሚያ ድርጅት፡፡
Dillmann, August(2005).*Ethiopic Grammar (2nd ed.).*USA(Oregon).Nipf &Stock Pubilshers.
Lambdin, Thomas (1978). *Introduction to classical Ethiopic (Ge'ez).* Michigan Edwards Brothers,Inc.
Leslow, Wolf (1987). *Conscience Dictionary of Geez*. Wiesbaden: Harvessawitz.
Ludolf, Hiob.1669. *Lexixcon Aethiopico-Latinum*. Frank furtiad Moenum: apud Johannem David Zunnerum.
Moscati, Sabatino et al (1964). *An Introdaction to the Comparative grammar of Sematic languages.* Wiesbden: Otto Harrassowitz. Printed in Germany.
Sergew Hble Sllasse (1972). *Ancient and Medieval Ethiopian history to 1270*. Addis Ababa: United printer.
Weninger (1999). *Ge'ez (Classical Ethiopic).*Newcastle.lirucom EUROP- Academic Publications. Wiesbden: Otto Harrassowitz.